www.abyssinialaw.com

# የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል

**ለለቅድመ ስራ ሰልጣኞች የተዘጋጀ**
**የስልጠና ሞጁል**

## የተሻሻለው ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት

በፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያወች ስልጠና ማእከል የተዘጋጀ

www.abyssinialaw.com

# ማውጫ

**መግቢያ** **ገጽ**

## ምዕራፍ አንድ

1. ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ መሰረታዊ ነጥቦች ------------ 4
1.1 ከውል ውጭ ስለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ምንነት ---------------------- 5
1.2 የኃላፊነት ምንጮች ------------------------------------------------------------ 6
1.3 ከውል ውጭ ስለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ዓላማ ----------------------- 7
1.4 የጉዳትና የካሳ ዓይነቶች -------------------------------------------------------- 7

## ምዕራፍ ሁለት

2. በጉዳት ኃላፊነት ዙሪያ የሚነሱ አከራካሪ ነጥቦች ------------------------------ 8
2.1 የጉዳት ካሣ ጠያቂዎች ----------------------------------------------------------- 9
2.2 ኃላፊነት የሚያርፍበት ሰው ማንነው? ------------------------------------------ 10

## ምዕራፍ ሶስት

ጉዳትና የጉዳት ዓይነቶች ______ 19
3. የጉዳት ምንነት ______ 19
**3.1 የጉዳት ዓይነቶች------------------------------------------------------------------ 20**
**3.1.1 ግልፅ የሆኑ ጉዳቶች------------------------------------------------------ 20**
**ሀ. የደረሱ ጉዳቶች------------------------------------------------------------- 20**
**ለ. ወደፊት የሚደርስ ጉዳት----------------------------------------------------- 21**
**3.1.2 የሕሊና ጉዳት-------------------------------------------------------------- 22**

## ምዕራፍ አራት

የጉዳት ካሳ (ኪሳራ) አከፋፈል ሥርዓት------------------------------------------- 24

4. ስለ ካሣ ምንነት በጠቅላላው------------------------------------------------------------ 24

4.1. ግልፅ የሆኑ ጉዳቶች የካሳ አከፋፈል ሥርዓት----------------------------------- 24

4.1.1. የተመዛዘነ (የተመጣጠነ) የካሳ አከፋፈል ሥርዓት----------------------------- 25

I. ተጐጂውን ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት አቋም (ሁኔታ) መመለስ--25

II. በምትክ ስለመካስ------------------------------------------------------------ 25

III. ሊገኝ ይችል የነበረውን ጥቅም በማመዛዘን ስለመካስ---------------------- 25

ለአካል ጉዳት እና ለሞት አደጋ ካሳ አከፋፈል------------------------------------------ 26

I.ለአካል ጉዳት ካሳ አከፋፈል---------------------------------------------------------- 27

1. የተቀጣሪ ሠራተኛ አካል ጉዳት-------------------------------------------- 27

ሀ. የደረሰውን የጉዳት መጠን ማገናዘብ------------------------------------- 27

ለ. ጉዳቱ በደረሰ ጊዜ የሠራተኛው ገቢ (ደሞዝ)---------------------------- 28

ሐ. የሠራተኛው በሥራ ላይ የሚቆይበት እድሜ-------------------------- 28

2. የራሱን ሥራ በመስራት የሚተዳደር ሰው --------------------------------- 28

3. ሥራ በመሥራት ላይ ያልነበረ ሰው ላይ የደረሰ የአካል ጉዳት------------ 30

II. የሞት አደጋ-------------------------------------------------------------------------- 30

4.1.2. የማይመጣጠን የካሳ አከፋፈል ሥርዓት---------------------------------------- 31

I. ተበዳዩ ጥፋት------------------------------------------------------------------------- 31

II. ርትዕን መሠረት በማድረግ ካሳ የሚወስንበት ልዩ ሁኔታ------------------------ 32

www.abyssinialaw.com

ሀ. ድርጊቱ ጥፋት መሆኑን ባለማወቅ የደረሰ ጉዳት------------------------ 33

ለ. በበላይ ትዕዛዝ ምክንያት የሚፈፀም ጥፋት---------------------------- 34

ሐ. ይደርሳል ተብሎ ሊታስብ የማይችል ጉዳት--------------------------- 35

መ. ስለግምት አስቸጋሪነት---------------------------------------------- 36

ሠ. አስፈላጊ ሁኔታ---------------------------------------------------- 37

ረ. የተቀጣሪ ሠራተኛ ሐላፊነት----------------------------------------- 38

4.2. ለሕሊና ጉዳት የካሳ አከፋፈል ሥርዓት-------------------------------- 38

4.3 በሌላ አኳኃን የመካስ ሥርዓት--------------------------------------------- 39

I. የተወሰደውን ነገር (ዕቃ) ሰለመመለስ----------------------------------- 40

II. በዓይነቱ ስለመተካት------------------------------------------------ 41

III. ስለክብርና ስለመልካም ዝና-------------------------------------------- 41

4.4 በውል ሕግና ከውል ውጭ የካሣ አሰላል________________________ 41

4.5 የወንጀል ተጠቂዎችና የካሣ ጥያቄ___________________________ 43

ማጠቃለያ_____________________________________________ 49

# መ ግ ቢ ያ

ከውል  ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ በፍርድ ቤት ውስጥ ብዙ አከራካሪና ውስብስብ ጥያቄዎች የሚነሱበት የሕግ ክፍል ነው፡፡ እለት ከእለት ከሚያጋጥሙ ይህን ሕግ የሚመለከቱ አስቸጋሪ ጉዳዮችና በሕጉ ክፍል ውስጥ ከሚገኙ አንፃራዊ ድንጋጌዎች የተነሳ ሕጉን ወጥ በሆነ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ሰፊ ጥናት ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ተረድተው ሕጉን ከነዓላማው ወጥነት ባለው መልኩ በመተግበር ረገድ በፍ/ቤቶች ውስጥ ከፍተኛ የግንዛቤ ጉድለት ይስተዋላል፡፡

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ዙሪያ በተደጋጋሚ የሚነሱ አከራካሪ ነጥቦችን ለውይይት በማቅረብ በአሰራር ላይ ያሉ ጉድለቶችን ጠቁሞ የመፍትሄ ሀሳቦችን በማመልከት ሰልጣኞች በሕጉና በአሰራር ዙሪያ የበለጠ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለማድረግና ለሕጉ ትኩረት በመስጠት ሰፊ ጥናት እንዲያደርጉ ለማነሳሳት ነው፡፡

በተግባር የሚያጋጥሙ ጉዳዮችን ለማሳየት የታቀደ ሥራ በመሆኑ ጽሁፉ የሕጉን አካዳሚ ወይንም ንድፈሃሳባዊ  ጉዳዮችን የሚዳስስ አይደለም፡፡

ስለሆነም የጽሑፉ የመጀመሪያው ምዕራፍ ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ መሰረታዊ ሐሳቦች የሚዳስስ ሲሆን ሁለተኛው ምዕራፍ የጉዳት ኃላፊነትን በተመለከተ የሚነሱ የመሰረታዊና የስነ ስርዓት ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

ሶስተኛው ምዕራፍ ጉዳትና ስለ ጉዳት መጠን ምዘናን በሚመለከት በሚነሱ ነጥቦች ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡ የመጨረሻው ምዕራፍ ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ዓላማ? በሆነው በካሣ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ሲሆን በዚሁ ክፍል ካሣን በማስላትና በመወሰን ረገድ የሕጉ ይዘትና በአሰራር ላይ የሚያጋጥሙ ጉዳዮች በሚገባ ይተነተናሉ፡፡

የጽሑፉን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሰልጣኞች ጽሑፉ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በማጥናትና በውይይት በማዳበር በየክፍሉ ስር የተነሱ ክንውኖቹንና ጥያቄዎችን በትኩረት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ መሠረታዊ ነጥቦች

በዚህ ክፍል ውስጥ ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ አጠቃላይ ጉዳዮች ለመንደርደሪያነት ያክል በአጭሩ ይብራራሉ፡፡ የክፍሉ ዓላማ ሰልጣኞች በሕግ ትምህርት ቤት ውስጥ ከውል ውጭ ስለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግን በተመለከተ በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ የተማሩትን ጠቅለል ባለመልኩ በማስቀመጥ በቀጣዩ ክፍሎች ውስጥ በጥልቀት ስለሚታዩ ጉዳዮች ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለማድረግ ነው፡፡

### 1.1 ከውል ውጭ ስለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ምንነት

በፍትሐብሔር ሕጋችን ከውል ውጭ ስለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ክፍል በመጀመሪያው ምዕራፍ ቁጥር 2027 ስር ኃላፊነትን ስለሚያስከትል ተግባርን ከመዘርዘር ውጭ የሕጉን ምንነት ትርጉም የሚሰጥ ነገር አናገኝም፡፡ ነገር ግን የሕጉ ስያሜ እንደሚያመለክተው ከውል ውጭ የሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ሶስት ሀሳቦችን ያዘለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ሀሳብ ከውል ውጭ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ጉዳት የሚለው ነው ሶስተኛው ደግሞ ለዚህ ጉዳት ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡ ስለዚህ ከነዚህ ሶስት ሀሳቦች በመነሳት ሕጉ የውል ግንኙነት ሳይኖር ወይም ውል ላይ ባልተመሰረተ ግንኙነት በአንድ በሕግ በተጠበቀ የሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት ሲደርስ ለዚህ ጉዳት ኃላፊነት የሚያርፍበትን አካል የሚለይና ጉዳቱ በካሣ መልክ እንዲስተካከል የሚያደርግ ሕግ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ሕጉ የውል ግንኙነትን የማይመለከት መሆኑን መግለጹ በመሰረቱም ሆነ በውጤቱ ከውል ሕግ የሚለይ የፍትሐብሔር ሕግ አካል መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን በጥቅም ወይም በመብት ላይ የሚደርስ ጉዳትን የሚመለከት ስለሆነ በጥቅም ወይም በመብት ላይ የሚደርስ ጥቃትን ከሚመለከት ከወንጀል ሕግ የተለየ ሕግ ነው፡፡

## 1.2 የኃላፊነት ምንጮች

በውል ግንኙነት ውስጥ የመብት ወይም የግዴታ ምንጭ የሰዎቹ ስምምነት ሲሆን ከውል ውጭ ለሚደርስ ኃላፊነት ደግሞ የግዴታው ምንጭ ሕግ ነው፡፡

በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2027 ስር እንደተዘረዘረው ሶስት ዓይነት የኃላፊነት ምንጮች አሉ፡፡የመጀመሪያው የኃላፊነት ምንጭ በራስ ጥፋት በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ወይም መብት ላይ ጉዳት ማድረስ ነው፡፡ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2029 ስር እንደተመለከተው ጥፋት ታስቦ ወይም በቸልተኝነት እንዲሁም ተግባርን በመፈጸም ወይም ባለመፈጸም ሊከሰት ይችላል፡፡

ጥፋት የተባሉ ጉዳዩች ከፍትሀብሄር ሕጉ ከቁጥር 2030 እስከ ቁጥር 2064 በዝርዝር የተቀመጡ ሲሆን እነኝህን ሕጉ ጥፋት ያላቸውን ነገሮች አውቆ አስቦበት ወይም በቸልተኝነት በማድረግ ወይም ባለማድረግ ፈጽሞ በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት ማድረስን የሚመለከትነው፡፡ በጥፋቱ ጉዳቱን ያደረሰው ሰው ተጐጂውን የመካስ የሕግ ኃላፊነት አለበት፡፡

ሁለተኛው የኃላፊነት ምንጭ ምንም ጥፋት ሳይኖር የሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት ሲኖር ነው፡፡ ይህ ኃላፊነት የሚመጣው ሕጉ ጥፋት ብሎ ከዘረዘራቸው ጉዳዩች ውጪ ጥፋት ባልሆነ ስራ ወይም የያዘው ወይም የራሱ የሆነ ነገር በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት የሚያደርሰውን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ኃላፊነትን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች በፍትሐብሄር ሕግ ከቁጥር 2066 እስከ 2089 በዝርዝር እንደተቀመጡት ራስን ወይም ሌላ ሰውን የራስን ወይም የሌላ ሰውን ሀብት በእርግጥ ሊደርስበት ከሚችል አደጋ ለማዳን ሲከላከል በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ፣ በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ፣ አንድ ሰው የያዘው ወይም የራሱ የሆነ የሚፈነዳ ወይም መርዝ የሚሆኑ ቅመማት፣ ከፍተኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ መስመር በመዘርጋት፣ የመሬት የተፈጥሮ መልክን በመቀየር አደገኛ የሆኑ የኢንዱስትሪ ስራዎችን በመስራት ጉዳት ሲደርስ፣ የራስ ወይም ለራሱ ጥቅም የያዘው እንስሳ ላይ ጉዳት ሲደርስ፣ አካል ላይ ጉዳት ሲያደርስ፣ የመኪና ጉዳት ሲያደርስ የተሰሩ እቃዎች ጉዳት ሲያደርሱ የሚመለከቱ ናቸው፡፡

በዚህ ሁኔታ ጉዳት ሲደርስ ተበዳይ የደረሰበትን ጉዳት ብቻ እንጂ ሕጉ ኃላፊ የሚያደርጋቸውን ሰዎች ጥፋት ማሳየት አይጠበቅበትም፡፡ እነሱም ጥፋት የለብንም ብለው መከራከር አይችሉም፡፡ ከኃላፊነት የሚያመልጡበት መንገድ ጉዳቱ የደረሰው በተበዳዩ ጥፋት መሆኑን በማሳየት ብቻ ነው፡፡

ሶስተኛው የኃላፊነት ምንጭ ደግሞ ሌላ ሰው ስለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊነት መውሰድን የሚመለከት ነው፡፡ የዚህ ኃላፊነት መሠረቱ የጉዳት አድራሹ ሰውና ኃላፊነትን የሚሸከመው ሰው ሕጋዊ ግንኙነት ነው፡፡ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2120 እስከ 2137 ከተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደምንረዳው ይህ ግንኙነት ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅና በቤተሰቡ ወይም በልጁ ጠባቂ ወይም አሳዳጊ፣ በአሰሪና በሰራተኛ ፣ በደራሲና በአሳታሚ መካከል ያለው ግንኙነት ነው፡፡

ጉዳት አድራሹ ሰው በጥፋቱ ወይም ጥፋት ሳይኖር በሚያደርሰው ኃላፊነት በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ሲያደርስ በሕጉ ላይ የተቀመጠው ሁኔታና ግንኙነት ሲኖር ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነትን የሚሸከመው በጉዳት አድራሹ ፋንታ ሕጉ ኃላፊ የሚያደርገው ሰው ነው፡፡

## 1.3 ከውል ውጭ ስለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ዓላማ

ከውል ውጭ ስለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ዓላማው የተጐዳ ሰውን መካስ ነው፡፡ በሌላ ክፍል እንደምንመለከተው የተጐዳውን ሰው ከጉዳቱ ጋር በሚመዛዘን መልኩ ወይም ልዩ የሆኑ ሁኔታዎች ለምሳሌ የተበዳዩ ጥፋትና በሌሎች ካሳን በርትዕ የሚያስወስኑ ነገሮች ሲያጋጥሙ ከጉዳቱ በታች ከሆነ ካሣ በመካስ ጉዳቱን ማስወገድ ወይም ማስተካከል ነው፡፡

### 1.3.1 የጉዳትና የካሣ ዓይነቶች

ጉዳት ማለት በሕግ በተጠበቁ መብቶች ወይም ጥቅሞች ላይ ኪሳራ ወይም ጉድለት መድረስ ማለት ሲሆን ወደፊት በሌላ ክፍል በሰፊው እንደምንመለከተው ጉዳት አሁን በግልጽ የሚታይ ወይም ለወደፊት በአርግጠኝነት የሚደርስ ወይም የማይታይ የሕሊና ጉዳት ሊሆን ይችላል፡፡

ጉዳት በፍትሐብሄር ሕጉ ቁጥር 2090 እና 2091 ስር እንደተደነገገው በመሰረቱ ተመጣጣኝ በሆነ ገንዘብ መጠን ነው የሚካሰው፡፡ ነገር ግን ጉዳቱ በአጋጣሚ ወይም በአእምሮ ሁኔታ ሊታሰብ በማይችል ሁኔታ የደረሰ ከሆነ እና የጉዳቱ መጠን ምን ያክል እንደሆነ ለማወቅ አዳጋች ከሆነ የነገሮችን ሁኔታዎች በማገናዘብ ፍ/ቤት በርትዕ ካሳን መወሰን እንዳለበት በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2101 እና 2102 ስር ተጠቅሶአል፡፡ ይህ የርትዕ ካሳ ርትዕ

ሲያስገድድ ከጉዳቱ መጠን በታችም መሆን ይችላል ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የሕሊና ጉዳትም ይህን ያክል ነው ተብሎ በገንዘብ መጠን ሊተመን ስለማይችል ካሳው በርትዕ ሆኖ የገንዘቡ ጣሪያም ከአንድ ሺህ ኢትዮጵያ ብር መብለጥ እንደሌለበት በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2116 /3/ ስር ተደንግጓል፡፡

በመረጃ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋሀድ ቁጥር 590/2000 አንቀጽ 41 /2/ ስር እንደተደነገገው ደግሞ በመገናኛ ብዙሃን ስመ አጥፊነት ምክንያት ለሚደርስ የሕሊና ጉዳት ከሰው እስከ አንድ መቶ ሺ የኢትዩጵያ ብር ሊደርስ እንደሚችል በልዩ ሁኔታ ተጠምጧል፡፡

የተወሰዱ እቃዎችን ከነጥቅማቸው ማስመለስና የተጎዱ እቃዎችን በዓይነት ማስተካት በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2118 እና 2119 ስር እንደ አማራጭ የካሣ ዓይነት ተቀምጧል፡፡

የደረሰው ጉዳት ከክብርና ከመልካም ዝና ጋር የሚያያዝ ከሆነ ከሣው ከፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2126 መሠረት በጉዳት አድራሹ ወጪ የስም ማደሻ ማስታወቂያ ማስለጠፍ ነው፡፡

ጉዳት እያስከተለ ያለ ድርጊት ወይም ጉዳትን የሚያስከትል ድርጊት ደግሞ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2121 መሰረት መፍትሔው በእግድ ማስቆም እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡

## የክንውን ጥያቄዎች

1. በአንድ ፍ/ቤት በቀረበ ጉዳይ ላይ ከሳሽ ተከሳሽ ከዚህ በፊት በሐሰተኛ ክስ ከሶኝ ክሱ ውድቅ ሆኖአል፡፡ያንን ክስ ለመከላከል ፍርድ ቤት በተመላለስኩበት ወቅት ከብቶቼን የሚጠብቅልኝ ሰው ስላልነበረ በአውሬ ተበልተውብኛል፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ በሐሰተኛ ክስ እኔን ፍ/ቤት በማመላለስ ከብቶቼ በአውሬ እንዲበሉ ስላደረገብኝ ካሣ ይከፈለኝ ብሎ ከሷል፡፡ይህ ጉዳይ ከውል ውጪ ስለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ምን መፍትሄ ይኖረዋል?
2. አንድ በወንጀል ተከሶ ለረጅም ጊዜ እስር ላይ የቆየ ሰው ፍ/ቤት በስተመጨረሻ ወንጀሉን የሚያስረዳ ተጨባጭ ማስረጃ አልቀረበበትም ብሎ ነፃ ሲያሰናብተው ተበዳይ ተብለው ባስከሰሱት ሰዎች ማስረጃ በሌለውና በሐሰተኛ ክስ አስከስሰውኝ ጉዳት እንዲደርስብኝ አድርገውኛል ስለዚህ ካሣ ይክፈሉኝ ብሎ ስከስ ተከሳሾች በበኩላቸው የወንጀል ከሳሽ እኛ ሳንሆን ዐቃቤ ሕግ ስለሆነ እኛ ልንከሰስ አይገባም ብለው ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ዳኛ ብትሆን ምን ትወስናለህ?

ከሣሹ የዐቃቤ ሕግ መስሪያቤትን በዚህ የፍትሃብሄር ጉዳይ ለመክሰስ የሕግ መሰረት ይኖረዋልን?

3. በሌላ ፍ/ቤት በቀረበ ጉዳይ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ላይ አህያ ተውሶ ልጁ ውሃ ቀድታ በአህያው ጭና እንድታመጣለት ይሰጣታል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሰውየው ልጅ አህያውን እየነዳች ውሃ ልትቀዳ ስትሄድ የሌላ ሶስተኛ ሰው ልጅ መንገድ ላይ መጥቶባት አህያዋን ከበስተኋላዋ በዱላ ሲመታት አህያዋ ዘላ አህያውን የተዋሰውን ልጅ ፊቷ ላይ በመርገጥ የፊት ጥርሶችዋን በመስበር ጉዳት ታደርሳለች፡፡

ለዚህ ጉዳት ኃላፊ የሚሆነው ሰው ማነው? በየትኛው ሕግ መሠረት?

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. በጉዳት ኃላፊነት ዙሪያ የሚነሱ አከራካሪ ነጥቦች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በጉዳት ኃላፊነት ዙሪያ የሚነሱ መሠረታዊና ስነ ስርዓታዊ የሆኑ የሕግ ጥያቄዎችን የሚዳስሱ ጉዳዮች ይተነተናሉ፡፡ የክፍሉ ዓላማ የጉዳት ካሣ ጥያቄን ማን እንደሚያቀርብና ጥያቄው ደግሞ በማን ላይ መቅረብ እንዳለበት ለማስገንዘብ ነው፡፡ ሰልጣኞች ከዚህ ክፍል የጉዳት ካሣን ማን ማግኘት እንዳለበትና እንደሌለበት፣ የጉዳት ኃላፊነት በማን ላይ እንደሚያርፍ በሚገባ ይረዳሉ፡፡

### 1.4 የጉዳት ካሣ ጠያቂዎች

በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2141 ስር እንደተመለከተው የደረሰበትን ጉዳት ልክና የጉዳት አድራሹን ኃላፊነት በማስረዳት ክስ ማቅረብ የሚችለው ጉዳቱ የደረሰበት ሰው ነው፡፡ጉዳት የደረሰበት ሰው ሲባል በሕጉ አነጋገር ተጐጂ የተባለው በቀጥታ ጉዳቱ ያረፈበት ሰው ወይም ይህ ሰው በመጐዳቱ ምክንያት በተዘዋዋሪ ጉዳቱ የሚያገኛቸው ሌሎች ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ /የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2095 እና 2144 ይመለከቷል/ ፡፡

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2142 መሰረት የካሣ ጥያቄ ከሣሽ የደረሰበትን ጉዳት ልክ ብቻ ሳይሆን የጉዳት አድራሹንም ኃላፊነት የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡

የፍትሐብሄር ኃላፊነት ከውል ወይም ከውል ውጭ ከሚኖር ግንኙነት ሊመነጭ ይችላል፡፡ የሁለቱም ውጤት ግን የተለያየ ነው፡፡ በውል ላይ ከተመሰረተ ግንኙነት የሚመነጭ ኃላፊነት በውል ሕግ መፍትሄ የሚያገኝ ሲሆን ከውል ውጭ የሚደርስ የፍትሐብሄር ኃላፊነት ደግሞ ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ይገዛል፡፡

በአሰራር ላይ የየሕጎቹን ልዩነት ካለመረዳት በውል ላይ በተመሰረተ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ለጉዳቱ የካሣ ጥያቄ ክሱን ከውል ውጭ በሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግን መሰረት በማድረግ የሚጠይቅበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ ጥያቄውን በውል ሕግ ወይም ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ማስተናገድ በአካሄድም ሆነ በውጤቱ ሰፊ ልዩነት አለው፡፡

አንድ ሰራተኛ በሥራ ላይ እያለ በሚደርስበት ጉዳት ቢሞት እሱ በመሞቱ የተጎዱ የሰራተኛው ቤተሰቦች የጉዳት ካሣ ክሳቸውን በአሰሪው ላይ ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግን መሰረት አድርገው ቢያቀርቡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱን እንዴት መምራት አለበት? ውጤቱስ ምን ይሆናል?

ሰልጣኞች ተወያዩበት፡፡

ባለሞተር ተሽከርካሪ ውል ሳይኖር በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት ሲያስከትል ጉዳዩ የሚመራው ከውል ውጭ በሆነ ኃላፊነት ሕግ /በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2081- 2084 / ባሉት ድንጋጌዎች ነው፡፡ በውል ላይ በተመሰረተ ግንኙነት በተለይ በሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት አግባብነት ያለው ሕግ የውል ሕግና የንግድ ሕግ ነው፡፡ ከውል ውጭ ተሽከርካሪዎች ለሚያደርሱት ጉዳት ባለንብረቱ ወይም ባለጥቅሙ ጥፋት ባይኖረውም እንኳን ለጉዳቱ ተመጣጣኝ ካሣ መክፈል ያለበት ሲሆን በውል ላይ በተመሰረተ የሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት በተሳፋሪው ወይም በጓዝ ላይ

ጉዳት ቢያደርስ ተዋዋዩ ጉዳቱ የደረሰው በራሱ ጥፋት ከሆነ ብቻ በንግድ ሕግ ቁጥር 636/1/ መሠረት እስከ አርባ ሺ የኢትዩጵያ ብር ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

አንድ በሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ተሳፍሮ እየሄደ ያለ ሰው ተሽከርካሪው በመገልበጡ ምክንያት በራሱና በጓዙ ላይ ጉዳት ቢደርስበት የካሣ ክሱን በውል ውጪ በሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ በተሽከርካሪው ባለቤት ላይ አቅርቦ የተሽከርካሪው ባለቤት ደግሞ ክሱ በዚህ ሁኔታ መቅረብ የለበትም ብሎ ቢቃወም መፍትሄው ምንድነው?

ሰልጣኞች ተወያዩበት፡፡

በፊት የክልል 14 መስተዳድር የዞን ፍ/ቤት ይባል በነበረው ፍርድ ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ/863/84 ላይ ከሳሾች እኛን የሚጦረን ልጃችን በተከሳሽ መሥሪያ ቤት መኪና ለስራ ሲጓዝ መኪናው ተገልብጦ ልጃችን ስለሞተ ተከሳሽ ከውል ውጭ በሆነ ኃላፊነት ካሣ ሊከፍለን ይገባል ብለው ክስ ሲያቀርቡ ተከሳሽ መስሪያ ቤት ባቀረበው መከራከሪያ በከሳሾች ልጅና በተከሳሹ መካከል የነበረው ግንኙነት የተመሰረተው በስራ ውል ላይ በመሆኑ የተከሳሾች ጥያቄ ሊስተናገድ የሚገባው በስራ ውል መሰረት እንጂ ከውል ውጭ በሆነ ኃላፊነት በሚመለከተው ሕግ ስላልሆነ ክሱ መዘጋት አለበት ብሏል፡፡

የዞኑ ፍ/ቤትም የተከሳሹን ተቃውሞ በመቀበል ክሱን ውድቅ ሲያደርግ ከሳሾች ውሣኔውን በመቃወም ይግባኝ ለጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ በመዝገብ ቁጥር 1525/88 ላይ የከሳሾችን ይግባኝ ውድቅ በማድረግ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንቷል፡፡
በፍ/ቤቶቹ ውሣኔ ትስማማለህ ? ለምን ?

በፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27/1/ መሰረት በሰው ላይ ወይም በሚንቀሳቀስ ንብረት ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት ካሳ የመጠየቅ ክስ የሚቀርበው ጉዳቱ በደረሰበት ስፍራ ለሚገኘው ፍ/ቤት ነው፡፡ በፍትሐብሄር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 24/2/ እና በንግድ ሕግ ቁጥር 647 መሠረት ደግሞ የሕዝብ ማመላለሻን ወይም ትራንስፖርትን

በተመለከተ ለሚደርስ ኃላፊነት ክስ የሚቀርበው ከሳሹ እንደመረጠ አጓገዥ በመደበኛ መኖሪያ ወይም ዋና ሥራው ባለበት ወይም ውሉን የተዋዋለው ወኪል ባለበት ወይም ዕቃና ጓዙ በሚደርስበት ቦታ ላለው ፍ/ቤት ነው፡፡

በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ተሳፍሮ ሲጓዝ የነበረ ሰው ተሽከርካሪው በመገልበጡ በራሱና በጓዙ ላይ ጉዳት ቢደርስበት የካሣ ጥያቄውን ለማስተናገድ ስልጣን ያለው ፍ/ቤት የትኛው ነው?

ከተያዘው ርዕስ ጋር ሊነሳ የሚገባው ሌላው ነጥብ የደረሰው ጉዳት ሞት ከሆነ በተጐጂው ላይ ከደረሰው የሞት አደጋ የተነሳ በራሳቸው ስም ሆነው በመተዳደሪያ ረገድ ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሣ ለመጠየቅ እንደሚችሉ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2095 ስር ተደንግጓል፡፡

ጉዳቱ ሞትን ባስከተለ ጊዜ ካሣ ሊከፈላቸው የሚገባ ሰዎችን ሕጉ በቁጥር 2095 ስር በዝርዝር በማስቀመጥ ከተዘረዘሩት ሰዎች ውጪ ሌሎች ሰዎች ምንም እንኳን በሞቱ ምክንያት መጐዳታቸውን ቢያስረዱም ካሳ እንደማይገባቸው በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2096 ስር ተጠቅሷል፡፡

ሕጉ በዝርዝር ካስቀመጣቸው ውስጥ " ወላዶቹ " የሚል ቃል አባትና እናትን ብቻ የሚያመለክት ነው ወይስ አያቶችንም ይጨምራል የሚል ጥያቄን ሊያስነሳ ይችላል፡፡የሕጉ የአማረኛው ድንጋጌ " ወላዶቹ "የሚለውን ቃል ሲጠቀም የእንግሊዘኛው ትርጉም ደግሞ (Ascendants and descendants )የሚለውን ተጠቅሞአል፡፡ የእንግሊዘኛው ትርጉም አያቶችንም የሚጨምር ሲሆን የአማረኛው ቃል ይህንን ይተካል አይተካም፣ " <u>ወላዶችና</u> " " <u>ወላጆች</u> " በሚለው ቃል መካከል ልዩነቱ ምንድነው የሚለው ጥያቄ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡

በአንድ ፍ/ቤት በቀረበ ጉዳይ አያቱን በመጦር የሚያስተዳድር ሰው በመኪና ተገጭቶ በመሞቱ ምክንያት አያቱ መተዳደሪያውን በማጣት ስለደረሰባቸው ጉዳት ካሳ ክስ ሲያቀርቡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ሕጉ በሞት ጊዜ በመተዳደሪያ ረገድ

ስለሚደርስባቸው ጉዳት በህጉ ካሳ የመጠየቅ መብት የተፈቀደው ለአባትና ለእናት እንጂ ለአያት አይደለም ብሎ ክሱን ዘግቶአል፡፡ የፍ/ቤቱ ውሳኔ እንዴት ይታያል?

በአዲሱ ቤተሰብ ሕግ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን ከነባሩ የፍትሐብሄር ሕግ ይልቅ የበለጠ ጥበቃ ተደርጐለታል፡፡ በእንዲህ ዓይነት አብረው በሚኖሩ ሰዎች በአንዱ ላይ በሚደርሰው የሞት አደጋ ምክንያት ሌላኛው ወገን በአንቀጽ 2095 ባል ወይም ሚስት የሚለውን ቃል በመጠቀም ካሳ መጠየቅ ይችላል ወይ? ሰልጣኞች ተወያዩበት፡፡

በአንቀጽ 2095/1/ ስር የተዘረዘሩ ሰዎች ተጐጂው በመሞቱ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ስር የካሳ ጥያቄን ሲያቀርቡ ተከሳሽ በበኩሉ እነዚህ ሰዎች የሟችን ሰፊ ንብረት በመውረስ እየተጠቀሙ መሆኑን በማስረዳት ቢከራከር ካሳ ከመክፈል ይድናል? ሰልጣኞች ተወያዩበት፡፡

በአንድ ፍ/ቤት በቀረበ ጉዳይ ሰፊ ንብረት የነበረው ሰው በመኪና ተገጭቶ ሲሞት የየራሳቸውን በቂ ኑሮ የነበራቸው የሟች ልጆች አባታችን በሕይወት በነበረበት ጊዜ የራሱን ንብረት ራሱ ያስተዳድር ነበር፡፡ አሁን እሱ በመሞቱ ምክንያት ያንን እሱ ያስተዳድር የነበረውን ንብረት ለማስተዳደር ሌላ ሰው ቀጥረን ለወጪ ስለተደረግን ይህንን ወጪአችንን ይክፈለን ብለው ጉዳቱን ባደረሰው መኪና ባለቤት ላይ ክስ አቅርበዋል፡፡ ከሳሾች ካሳውን ሊያገኙ ይችላሉ? በየትኛው ሕግ መሠረት?

በአንቀጽ 2095 /1/ ስር በመተዳደሪያ ረገድ ካሳ የመጠየቅ መብት ያላቸው ሰዎች የካሳ ጥያቄዎቻቸው ለየብቻ ይስተናገዳል ወይስ የአንዱ መኖርና ካሳን መጠየቅ ሌላውን ካሳ ከመጠየቅ ያግደዋል?

## 1.5 <u>ኃላፊነት የሚያርፍበት ሰው ማን ነው</u>?

ከውል ውጭ ለሚደርስ ጉዳት ሕጉ ኃላፊ የሚያደርጋቸው ሰዎች ጉዳቱን በካሳ ለማስተካከል ኃላፊነት አለባቸው፡፡ እነዚህን ሕጉ ለጉዳት ኃላፊ የሚያደርጋቸውን ሰዎች ለይተው ኃላፊነቱን እንዲሸከም ማድረግ ላይ በተግባር ላይ ሲያስቸግር ይስተዋላል፡፡ለምሳሌ አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ እየሄደ እያለ ጉዳት ብያደርስ

ጉዳቱ የደረሰበት ሰው የተሽከርካሪውን ባለቤት ወይስ አሽከርካሪውን ወይስ ሁለቱንም አንድ ላይ መክሰስ አለበት የሚለው ጥያቄ ብዙ ጊዜ ያጋጥማል፡፡

ለእንደዚህ ዓይነት ጉዳት ኃላፊነት ማን ላይ ያርፋል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መደበኛና የስነ ስርዓት ሕጉን በሚገባ ማጤንን ይጠይቃል፡፡

በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2081/1/ መሰረት መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ለሚያደርሰው ጉዳት ባለቤቱ ኃላፊ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ የተሽከርካሪው ባለቤት ከዚህ ኃላፊነት ማምለጥ የሚችለው በቁጥር 2081/2/ መሰረት መኪናው ጉዳቱን ባደረሰበት ጊዜ የተሰረቀበት መሆኑን ወይም በቁጥር 2082 መሠረት ተሽከርካሪው ጉዳቱን ባደረሰበት ጊዜ ለሌላ ሰው ጥቅም ሌላ ሰው እጅ የነበረ መሆኑን ወይም በቁጥር 2086/2/ መሠረት ጉዳቱ የደረሰው በተጐጂ ሙሉ ጥፋት መሆኑን ካስረዳ ብቻ ነው፡፡

በመኪናው ስለባለቤቱ ወይም ስለሌላ ሰው ጥቅም የሚሰራ ሰው ጥፋት ካልሰራ በስተቀር መኪናው ስለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂ እንደማይሆን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2082/2/ ስር ተደንግጓል፡፡

የተሽከርካሪው ባለቤት ተበዳይን ተገዶ ከካሰ በኃላ በቁጥር 2082/2/ ስር የተጠቀሰውን ጥፋት በማስረዳት ከመኪናው ጠባቂ የከፈለውን ኪሳራ ማስመለስ እንደሚችል በቁጥር 2083/1/ /2/ ስር ተጠቅሷል፡፡

በተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበት ሰው ለደረሰበት ጉዳት ካሳ የተሽከርካሪውን ባለቤት ብቻ መክሰስ አለበት ወይስ በሕጉ አነጋገር ለባለቤቱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም የሚሰራ በተለምዶ ሾፌር ተብሎ የሚጠራውንም ጨምሮ መክሰስ አለበት? ከሳሹ የመኪናውን ባለቤትና ሾፌሩን አንድ ላይ ቢከስ ፍ/ቤት ሁለቱም ላይ በአንድነት ጉዳቱን እንዲክሱ ሊወስን ይችላል?
ሰልጣኞች የፍትሐብሄር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33/3/ እና 36ትን እላይ በተጠቀሱት ከፍትሐብሄር ሕግ ቁጥሮች ጋር በማየት በእነኚህ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩበት፡፡

የክልል 14 መስተዳድር ዞን ፍ/ቤት ይባል ለነበረው ፍ/ቤት በቀረበ አንድ ጉዳይ ላይ ከሳሽ በመንገድ ላይ እየሄደ እያለ የሁለተኛ ተከሳሽ መኪና የአንደኛ ተከሳሽ መኪናን ከኋላው በመግጨቱ ምክንያት የአንደኛ ተከሳሽ መኪና ከመንገድ ወጥቶ ጉደት ስላደረሰብኝ ካሳ ይክፈለኝ ብሎ የሁለቱንም መኪኖች ባለቤትና ሾፌሮቻቸውን አጣምሮ ሲከስ አንደኛ ተከሳሽ መኪናዬ ጉዳቱን ያደረሰው በሁለተኛ ተከሳሽ መኪና ምክንያት ነው ብሎ ስለተከራከረ ጉዳዩን የመረመረው ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 1359/82 ላይ ጉዳቱ የደረሰው የሁለተኛ ተከሳሽ መኪና የአንደኛ ተከሳሽ መኪናን ከኋላው ስለገጨ ሁለተኛ ተከሳሽና ሹፌሩ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናቸው ብሎ ወስኖአል፡፡

ይህ ጉዳይ በይግባኝ የቀረበለት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ.ብ.የ.መ.ቁ. 1941/88 ላይ ጥፋት ሳይኖር ከውል ውጪ ለሚደርስ ጉዳት አንደኛ ተከሳሽ የሁለተኛ ተከሳሽ መኪናን ግጭት ምክንያት በማድረግ ከደረሰው ጉዳት ማምለጥ የሚያስችለው ሕግ የለም በማለት ለደረሰው ጉዳት አንደኛ ተከሳሽን ኃላፊ አድርጎታል፡፡

ከሁለቱ ፍ/ቤቶች ውሳኔ በየትኛው ትስማማለህ ? ለምን?

በጠቅላይ ፍ/ቤት የተወሰነበት አንደኛ ተከሳሽ የተወሰነበትን ገንዘብ ለማስመለስ በሁለተኛ ተከሳሽ ላይ ክስ ቢከፍት ጉዳዩ ምን የሚሆን ይመስልሃል? ሰልጣኞች ተወያዩበት፡፡

ባለቤቱ በማያውቅበት ወይም ባልፈቀደበት ሁኔታ ለትራንስፖርት ሳይሆን በሌላ ሥራ ለተሰማሩ ተሽከርካሪዎች ላይ በተለምዶ ሾፌሮች ከመንገደኛ ጥቅም በመቀበል አሳፍሮአቸው ሲሄዱ ተሽከርካሪው በመገልበጥ ወይም በመጋጨት ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ በመኪና ላይ ተሳፍረው እየሄዱ እያለ መኪናው በመገልበጡ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ለደረሰባቸው ጉዳት ካሣ በተሽከርካሪው ባለቤት ላይ ክስ ሲያቀረቡ ጠቅላይ ፍ/ቤት በ.መ.ቁ. 1854/88 እና 9881 ላይ የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2089 በመጠቀም ክሱን ውድቅ አድርጎባቸዋል፡፡

ይህ ከሆነ የከሳሾች ጉዳት መፍትሄው ምንድነው፡፡ ሰልጣኞች ከሳሾች የሕግ ምክር ቢጠይቁአችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

ከዚህ ርዕስ ጋር ሊነሳ የሚገባ ሌላው ነጥብ ሶስተኛ ሰዎችን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ጋር ተያይዘው በስፋት የሚነሳ የሶስተኛ ወገን ክርክር ኢንሹራንስን የሚመለከት ነው፡፡

ኢንሹራንስ አንድን ጉዳት በተመለከተ በሚሰጠው የመድን ሽፋን ምክንያት የተባለው ጉዳት በደረሰ ጊዜ ወደ ጉዳዩ ሊገባ ይችላል፡፡ በዚህ መሠረት እላይ እንደተመለከተው አንድ ተሽከርካሪ ጉዳት ቢያደርስ ይህ ተሽከርካሪ ላደረሰው ጉዳት የመድን ሽፋን ያለው ከሆነ ጉዳቱ የደረሰበት ሰው በሕጉ መሠረት የተሽከርካሪውን ባለቤት በበኩሉ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆን ከሆነ ከኢንሹራንስ ጋር ባለው ውል መሰረት ኢንሹራንስ በክርክሩ ውስጥ ገብቶ ኃላፊነቱን ተክቶ ካሳ እንዲሸፍንለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

እዚህ ላይ በተግባር ብዙ ጊዜ አከራካሪ ሆኖ የሚታየው ነጥብ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገው ኢንሹራንስ በክርክሩ ውስጥ ያለው ድርሻ ምንድነው የሚለው ነው፡፡

አንዳንድ ሰዎች ኢንሹራንስ ወደ ክርክሩ የሚገባው ከከሳሽ ጋር ባለው የሕግ ግንኙነት ሳይሆን ከተከሳሽ ጋር ባለው የውል ግንኙነት ምክንያት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ኢንሹራንስ ከከሳሽ ጋር የሚያከራክረው ጉዳይ አይኖረውም፡፡ ክርክር ካለውም በውሉ መሠረት ከተከሳሽ ጋር እንጂ ከከሳሽ ጋር የውልም ሆነ ከውል ውጭ ግንኙነት ስለሌለው ከሳሽን የመከራከር የሕግ መንገድ የለውም ይላሉ፡፡

ሌሎች ደግሞ ተከሳሽ ኃላፊ የሚሆን ከሆነ በስተመጨረሻ ካሳውን የመክፈል ኃላፊነት የሚያርፈው በኢንሹራነስ ላይ ስለሆነ ከሳሽን የመከራከር መብቱ ሊጠብበት አይገባም፡፡ በንግድ ሕጉ ላይም ኢንሹራንስ የፍትሐብሄር ክርክሩን ይመራል የሚለው ይህንኑ የሚመለከት ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡

ሰልጣኞች ሁለቱንም ሀሳቦች በሚገባ በማጤን የትኛው ሃሳብ የሕጉን መንፈስ የተከተለ መሆኑን አብራሩ፡፡

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ.ይ.መ.ቁ. 1113 ላይ በይግባኝ በቀረበለት አንድ ክርክር በስር ፍ/ቤት ከሳሽ በተከሳሽ መኪና ተገጭቼ ጉዳት ስለደረሰብኝ ተከሳሽ ካሳ ይክፈለኝ ብሎ ሲከስ ተከሳሽ በበኩሉ መኪናው የመድን ሽፋን ስላለው በመካከላቸው ባለው የኢንሹራንስ ውል መሠረት የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

በጉዳዩ ውስጥ ተካፍሎ ድርሻውን እንዲከፍልለት ስለጠየቀ የስር ፍ/ቤትም የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በክርክሩ ውስጥ እንዲካፈል በማድረግ የተከሳሽ መኪና ከሳሽ ላይ ካደረሰው ጉዳት ውስጥ በመድን ውል ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ መድን ድርጅቱ ተከሳሽን ተክቶ ለከሳሽ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅትም የከሳሽ ክርክሮችንና የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሲያቀርብ የስር ፍ/ቤት ከሳሽ የነበረው መልስ ሰጪ ይግባኝ ባይ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከተከሳሽ ጋር በነበረው የኢንሹራንስ ውል መሰረት የተከሳሽን የካሳ ድርሻ ለመክፈል በሶስተኛ ወገን ተከፋይነት ወደ ክርክር የገባ ስለሆነ ተከሳሽን ተክቶ ከሳሽን ሊሟገት አይችልም፡፡

በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 43/3/ መሰረት ሶስተኛ ወገን ከተከሳሽ ጋር ባለው የመብት ጥያቄ ምክንያት ወደ ክርክሩ የሚገባ ስለሆነ ከከሳሽ ጋር ምንም ግንኙነትም ሆነ ክርክር ስለማይኖረው ከሳሽን ሊከራከር አይገባም፡፡ ከተከሳሽ ጋር ድርሻውን እንዲካፈል ከተወሰነበትም ተከሳሽ ሳይሆን ከሳሽን ለመሟገት ይግባኝ ሊፈቀድለት ስለማይገባ ይግባኙ ውድቅ ሊሆን ይገባል ብሎ ተከራክሮአል፡፡

የመልስ ሰጪ መከራከሪያ ተቀባይነት አለው የለውም? ሰልጣኞች ሕጋዊ ምክንያቶችን በማስቀመጥ ለዚህ ክርክር የውሳኔ ሃሳብ ስጡበት፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# ጉዳትና የጉዳት አይነቶች

የዚህ ክፍል አላማ ሰልጣኞች ከውል ውጭ የሚደርስ ጉዳት ምንነት፣ የጉዳት አይነቶች፣ የጉዳት መጠንን ማረጋገጥ በማስመልከት በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ ነው፡፡

## 3. የጉዳት ምንነት

ከውል ውጭ የሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ህጋችንን ስንመለከት የጉዳት አይነቶች ከመዘርዘራቸው ባሻገር ጉዳት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተቀመጠ ትርጉም የለም፡፡ ነገር ግን ህጉ ጉዳት ብሎ ያስቀመጣቸው ጉዳቶች ሲታዩ ጉዳት ማለት በሰው ጥቅም ወይም ሀብት ላይ የሚደርስ ጉድለት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በህጉ ላይ ማብራሪያ የፃፉት ፕሮፌሰር ጆርጅ ቺቺኖቪችም ጉዳት በሰው ጥቅም ላይ የሚደርስ ኪሳራ ነው የሚል ትርጉም ሰጥተውታል፡፡

## 3.1 የጉዳት ዓይነቶች

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ጉዳት በሰው ጥቅም ወይም ሀብት ላይ የሚደርስ ኪሳራ ወይም ጉድለት ነው፡፡ ይህ የሰው ጥቅም በገንዘብ የሚተመን ወይም የማይተመን ሊሆን ይችላል፡፡ በገንዘብ የሚተመን ጥቅም ላይ የሚደርስ ኪሳራም በገንዘብ መጠን ሊታወቅ የሚችል ሲሆን በገንዘብ የማይተመን ጥቅም ላይ የሚደርስ ጉዳትን በገንዘብ መጠን ተምኖ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም በፍትሐብሄር ህግ ውስጥ ጉዳት ግልጽ የሆኑ ጉዳቶችና የህሊና ጉዳት በመባል ለሁለት ተከፍሎ ተቀምጧል፡፡ (የፍ/ህ/ቁ/2090 እና 2105) በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ እንደምንመለከተው ህጉ ለጉዳት የሚከፈለው ካሳ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመዛዛኝ ወይም ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ የካሳ ልክን ለመወሰን የጉዳት አይነቶች ለይቶ ማወቁ አስፈላጊ ስለሆነ እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን፡፡

### 3.1.1፡- <u>ግልፅ የሆኑ ጉዳቶች</u> (Material Damage)

ጉዳት የደረሰበት ወገን ከሚደርስበት ጉዳቶች አንዱ፣ የተጐጂውን ንብረት ወይም የገንዘብ ጥቅም በቀጥታ የሚመለከት ሊሆን ይችላል:: ይህም ማለት ጉዳቱ በቀጥታ ንብረቱ ላይ የደረሰ ከሆነ በጉዳት ምክንያት ንብረቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከጥቅም ውጭ ከሆነ ይኸው ንብረት ያለውን ዋጋ የሚመለከት ሲሆን ፣ ወይም አንድ ሰው በደረሰበት የአካል ጉዳት ሳቢያ ለሕክምና ያወጣወ ወጪ ወይም በደረሰበት ጉዳት ሳቢያ ሥራ ባለመስራቱ ያጣው ገቢ ወደፊት ሊያጣ የሚችለውንም ይጨምራል:: እንደነዚህ ዓይነት ጉዳቶች በሕጉ ግልፅ ጉዳቶች የሚባሉት ናቸው::

ግልፅ የሆኑ ጉዳቶች የደረሱ ጉዳቶች ወይም ወደፊት ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶች ተብለው ይከፈላሉ::

### ሀ. <u>የደረሱ ጉዳቶች፡-(Present Material Damage)</u>

ይህ ማለት ጉዳት በመድረሱ በተጐጂው ላይ በእርግጠኝነት የደረሰውን የገንዘብ ኪሳራ ለማመልከት ነው:: <u>ለምሳሌ፡-</u> አንድ የአካል ጉዳት የደረሰበት ሰው ለሕክምና ያወጣው ወጪ እንደዚሁም የንብረት ጉዳት የደረሰበት ሰው በጉዳቱ ምክንያት የንብረቱ ዋጋ መቀነስ ወይም ሙሉ ለሙሉ ዋጋ ማጣት ጉዳት ሊሆን ይችላል::

ስለዚህ አንድ ተጐጂ በአካሉ ላይ ለደረሰበት ጉዳት ለሕክምና 500 (አምስት መቶ ብር) ወጪ ካደረገ 500 መቶ ብር የደረሰ ጉዳት ነው:: እንደዚሁም አንድ ንብረት ለምሳሌ መኪና ላይ ከፍተኛ የግጭት አደጋ በመድረሱ ከጉዳቱ በፊት 40.000 (አርባ ሺህ ብር) ዋጋ የነበራት መኪና ከግጭቱ ብኃላ ዋጋዋ 25.000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) ከሆነ በባለንብረቱ ላይ የ15.000 (አስራ አምስት ሺህ ብር) ጉዳት ደርሶበታል ማለት ነው:: በተጨማሪም አንድ በቀን ሥራ በመተዳዳር ላይ የሚገኝ ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት ደርሶበት ለተወሰነ ጊዜ ለምሳሌ ለ10 ቀን ሥራ መስራት ካልቻለ የ10 ቀን ገቢ ተቋርጦበታል ማለት ነው:: ስለሆነ በቀን የሚያገኘው ገቢ ተስልቶ ለምሳሌ የቀን ገቢው 15 ብር ከሆነ በ10 ቀን 150 ብር ገቢ አቷል ማለት ነው:: ይህም የደረሰ ጉዳት ይባላል::

### ለ. <u>ወደፊት የሚደርስ ጉዳት</u> (Future Damage)

በጉዳት ምክንያት ተጉጂው ለወደፊቱ የሚያጣው ወይም የሚያወጣው ወጪን የሚመለከት ነው:: ለምሳሌ፣ አንድ ሾፌር በደረሰበት ጉዳት ሳቢያ ሽባ ከሆነ እንደቀድሞው ሠርቶ ገቢ የማግኘት እድል የለውም ሊባል ይችላል ሰለሆነም ከጉዳቱ በፊት ያገኝ የነበረውን ገቢ ለወደፊቱ ያጣ ስለሚሆን ወደፊት የሚደርስ ግልፅ ጉዳት ደርሶበትል ይባላል:: በሌላ ምሳሌ፣ አንድ ጉዳት የደረሰበት ሰው በጉዳቱ ምክንያት ለወደፊቱም ዘላቂ የሆነ ሕክምና ያስፈልገዋል ተብሎ በሕክምና ባለሞያዎች ከተረጋገጠ ለወደፊቱ ለሕክምና ወጪ ማውጣቱ የማይቀር ሐቅ ይሆናል:: ስለሆነም ወደፊት የሚደርስ ግልፅ ጉዳት ደርሶበታል ማለት ነው::

በአጠቃላይ ግልጽ የሆኑ ጉዳቶች (የደረሰ ጉዳትና ለወደፊት የሚደርስ ጉዳት) ካሳ ሊያስከፍሉ የሚችሉ በእርግጠኝነት የሚታዩ ሲሆን ብቻ ነው። (የፍ/ሕ/ቁ/ 2102(2) እና 2092) እነዚህ ጉዳቶች መኖራቸው የሚረጋገጠው በማስረጃ ሲሆን በፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 2041 መሰረት ተጎጂው ህጋዊ ማስረጃን በማቅረብ የደረሰበትንና ለወደፊት የሚደርስበትን ጉዳት ማረጋገጥ ይኖርበታል። ተከሳሹ ጉዳቱን በግልጽ ባያስተባብልም እንዳመነ ተቆጥሮ ማስረጃ ያልቀረበበት ጉዳት ካሳ ሊወሰንለት ስለማይችል ከሳሹ ጉዳቱንና የጉዳትንና የጉዳት መጠኑን የሚያሳይ ማስረጃ አቅርቦ ማረጋገጥ አለበት (የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 83)

የደረሰ ጉዳትን በተመለከተ ጉዳት መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ባያስቸግርም አንዳንድ ጊዜ የጉዳቱን መጠን የሚያመለክት ማስረጃን ማግኘት አዳጋች ይሆናል። በዚህ ጊዜ ተጎጂው ጉዳት መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ከቀረበና የጉዳት መጠኑን ማወቅ አስቸጋሪ ከሆነ ጉዳቱን ካሳ በረትዕ እንዲወስን ለፍ/ቤት ስልጣን ተሰጥቶታል (የፍ/ህ/ቁ/ 2102(1)) የወደፊት ጉዳት ደግሞ ማንም ሰው ለወደፊት ሊደርስ የሚችለውን ነገር በፍጹም እርግጠኝነት ማወቅ ስለማይችል በህጉ ላይ ለወደፊት ሊደርስ የሚችለው ጉዳት የተረጋገጠ ሲሆን የሚለው ሐረግ ፍጹም እርግጠኝነት (absolute certainty) ሳይሆን ምክንያታዊ እርግጠኝነትን (Reasonable certainty) የሚያመለክት ነው።

## 3.1.2:- የሕሊና ጉዳት (Moral Damage)

የሕሊና ጉዳት የተጉጂውን የገንዘብ ጥቅም ወይም ኪሱን የሚጐዳ ሳይሆን የተጉጂውን የስሜት መጉዳት ከግንዛቤ የሚያስገባ ነው:: ይኸውን በጉዳቱ ምክንያት በተጉጂው የደረሰው የስሜት መጉዳት፣ሐዘን፣ሐፍረት ወዘተ... መጉዳቱን መሠረት በማድረግ እንደ ጉዳቱ ዓይነትና ደረጃ የሕሊና ጉዳት ካሳ ሊከፈለው ይችላል::

ለምሳሌ:- በአንድ ሰው ላይ የአካል ጉዳት በመድረሱ በገንዘብ ረገድ ከሚደርስበት ጉዳት ማለትም ከግልፅ ጉዳት በተጨማሪ አካሉ በመጉደሉ፣ በሰውነቱ ላይ ነባሪ የሆነ ምልክት (ጠባሳ) በመቅረቱ ወዘተ...ስሜት መጉዳቱ የማይቀር ነው:: ይህን የስሜት መጉዳት በገንዘብ ለማስላት አስቸጋሪ ወይም የማይቻል ቢሆንም ጉዳቱን ለማስታገስ ወይም ለማቃለል በሕጉ በተቀመጠው መሠረት የሕሊና ጉዳት ካሳ በገንዘብ ሊከፈለው ይችላል::

# የውይይት ጥያቄዎች

1. በአንድ ፍርድ ቤት በቀረበው ጉዳይ ላይ ከሳሽ ተከሳሽ ባደረሰብኝ የአካል ጉዳት ምክንያት ለሕክምና፣ ከጉዳቱ ለማገገም ለምግብና ለአስታማሚ ያወጣሁት ወጪዎች ይከፈለኝ ብሎ ከሶ ተከሳሽ የአካል ጉዳት እንዳደረሰበትና በዚህ ምክንያት ሐኪም ቤት ሄዶ መታከሙን የሚያሳይ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ነገር ግን ለሕክምና፣ ለምግብ እና ለአስታማሚ ምን ያህል ወጪ እንዳወጣ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተከሳሹ በጉዳቱ ምክንያት ምን ያህል ወጪ እንዳወጣ የሚያሳይ ማስረጃ ባያቀርብም መጐዳቱንና መታከሙን የሚያሳይ ማስረጃ ስላቀረበ በዚህ ሀገር ሰዎች ላወጡት ወጪ ደረሰኝ የመቀበል ልምድ ስላልዳበረ ጉዳቱን የታከመ ሰው ለሕክምና ወጪ ማውጣቱን እንዲሁም የተጐዳ ሰው ከጉዳቱ ለማገገም ከተለመደው የተለየና ተጨማሪ ምግብን በመጠቀም ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉ ስለማይቀር ብሎ ምክንያት በማስቀመጥ ለከሳሽ በግምት ካሣ ቆርጦለታል፡፡

ሠልጣኞች በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ትስማማላችሁ? ለምን?

2. በሌላ ፍ/ቤት በቀረበ ጉዳይ ደግሞ በእርሻ ሥራ ላይ የተሰማራ ከሳሽ ተከሳሽ በእግሬና በእጄ ላይ በደረሰብኝ ቋሚ የአካል ጉዳት ምክንያት የእርሻ ሥራዬን አሁን መሥራት ስለማልችል እርሻዬን እያረስኩኝ አገኝ የነበረውን ገቢዬን አሁን ተከሳሽ ሊከፍለኝ ይገባል ብሎ ተከራክሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ የከሳሽ ጉዳት ምንድነው? ካሳስ እንዴት ይታሰብለታል?

3. መኪናው በሌላ መኪና ጥፋት ምክንያት ተገጭቶ የተጐዳችበት ሰው መኪናውን ለማሠራት ከሚያወጣው ወጪ በተጨማሪ መኪናው እስክትሰራ ድረስ በመኪናው ያገኝ የነበረውን ገቢ መጠየቅ ይችላል? ለምን

ይህ መኪናው የተገጨችበት ሰው መኪናው እስክትሰራ ድረስ ሌላ መኪና ተከራይቶ በመሥራት ለሌላ ወጪ ከተዳረገ ወጪው ሊተካለት ይችላል? ለምን

4. በሌላ ፍ/ቤት በቀረበው የካሣ ክስ የ12 ዓመት ልጅ በመኪና ግጭት የሞተበት አባት ልጁን እስከዚያ ጊዜ ድረስ ለማሳደግ ያወጣውን ወጪ ጠይቋል፡፡

ሠልጣኞች ለዚህ ጥያቄ ሕጋዊ አስተያየት ስጡበት?

# ምዕራፍ አራት

# የጉዳት ካሳ (ኪሳራ) አከፋፈል ሥርዓት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከውል ውጭ ለሚደርስ ጉዳት ካሣው እንዴት ተሰልቶ እንደሚከፈል እንመለከታለን፡፡ የክፍሉ ዓላማ ካሣን በማስላት ረገድ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለባቸውን ነጥቦች ሰልጣኞች በትኩረት እንዲገነዘቡ ለማድረግ ነው፡፡

## 4. ስለ ካሣ ምንነት በጠቅላላው

በዚህ ጽሁፍ ምዕራፍ አንድ ውስጥ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ከውል ውጭ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ዓላማው ከውል ግንኙነት ውጭ በሆነ ሁኔታ በአንድ ሕግ በተጠበቀ መብት ላይ ጉዳት ሲደርስ ጉዳት አድራሹ ወይም ለጉዳቱ ሕጉ ኃላፊ የሚያደርገው ሰው ጉዳቱን በመካስ እንዲያስተካክለው ማድረግ ነው፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ከውል ውጭ ስለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ክፍል ውስጥ የካሣ ዓይነቶችና ስሌት ከመዘርዘሩ ውጪ ለካሳ ትርጉም አልተቀመጠለትም፡፡

ነገር ግን ከፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2090 /1/ እና 2091 ስር ከተቀመጠው ድንጋጌ ካሳ ለአንድ ጉዳት ለደረሰበት ሰው የጉዳት መጠኑ ተተምኖ ለዚያ ጉዳት መጠን የሚሰጠው ጥቅም ወይም ገንዘብ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ይህ ለተጐጂው የሚሰጠው ጥቅም ለጉዳቱ ፈንታ ሆኖ ጉዳቱን ለማስተካከል ሲባል ነው፡፡

ከዚህ በኋላ እንደምንመለከተው የካሳ ዓይነቶች የተለያዩ ቢሆኑም ዋንኛው የካሳ ዓይነት ከጉዳቱ ጋር ተመዛዛኝ የሆነ በገንዘብ የመካስ ዘዴ ነው፡፡

## 4.1:- ግልፅ ለሆኑ ጉዳቶች የካሳ አከፋፈል ሥርዓት

( Modes and Extent of Compensation For Material Damage)

ግልፅ የሆኑ ጉዳቶችን የደረሰ ጉዳት ወይም ወደፊት የሚደርስ ጉዳት በሚል ከፋፍለን አይተናቸዋል:: ግልፅ የሆኑ ጉዳቶች የካሳ አከፋፈል ሥርዓት ሁለት መሰረታዊ መርሆዎችን (ደንቦችን) የሚከተል ነው::

የመጀመሪያው ተመዛዛኝ (ተመጣጣኝ) የካሳ አከፋፈል ሥርዓት ሲሆን ይኸውም በጉዳቱ ተጉጂ የሆነ ወገን ከጉዳቱ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ ማድረግ፣ ለደረሰበት ጉዳት በምትኩ የገንዘብ ካሳ እንዲከፈለው የማድረግና ወይም ሊገኝ ይችል የነበረውን ጥቅም (ትርፍ) በማመዛዘን የሚከፈል የካሳ ዓይነቶች ተብለው ሊቀመጡ ይቻላል::

ሁለተኛው ደንብ የማይመጣጠን የካሳ፣ አከፋፈል ሥርአት ሲሆን ይኸውም የተጉጂውን ጥፋት በማገናዘብና በርዕት የሚከፈለውን የሚያጠቃልል ነው::

### 4.1.1:- የተመዛዘነ (የተመጣጠነ) የካሳ አከፋፈል ሥርአት

(The  Equivalence Rule)

ይህ የካሳ አከፋፈል ሥርአት በተለይ ግልፅ ለሆኑ ጉዳቶች የካሳ አከፋፈል በጣም ጠቃሚ ነው:: **የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 2091** ድንጋጌን ስንመለከት ለደረሰው ጉዳት ሐላፊ ሆኖ የተገኘው ሰው ለተጉጂው የሚከፍለው ካሳ በተጉጂው ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን እንዳለበት ያመለክታል:: ስለሆነም በተጉጂው ላይ የደረሰው የጉዳት መጠን መታወቅ ይኖርበታል ::

በተጉጂው ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን በሚከተሉት መንገዶች (ሥልቶች) መመርመር ይቻላል::

I. <u>ተጉጂውን ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት አቋም (ሁኔታ) መመለስ</u>

<u>(Reinstatement):-</u>

በዚህ መንገድ (ስልት) ተጉጂውን ለመካስ የተጉጂውን ከጉዳቱ በፊት የነበረው ሁኔታ ማወቅ ያስፈልጋል:: <u>ለምሳሌ:-</u> በተጉጂው መኪና ላይ ጉዳት ደርሶ ከሆነ መኪናው እንዲጠገንለት ማድረግ፣ መኪናው ሙሉ በሙሉ ወድሞ (ጠፍቶ) ከሆነ ለተጉጂው አንድ አይነት የሆነ ሌላ መኪና እንዲያገኝ በማድረግ መካስ ሲሆን ይህም የደረሰን ጉዳት ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ይረዳል:: አንድ አንድ  ጊዜ ደግሞ ተጉጂው የደረሰበትን ጉዳት

ለምሳሌ:- በመኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት ብንመለከት ተጐጂው በራሱ ወጭ መኪናውን ሊያስጠግን ወይም ሙሉ በሙሉ ወድሞ (ጠፍቶ) ከሆነም በሌላ መኪና በራሱ ወጭ ተክቶ ከሆነ ለጉዳቱ ሐላፊ የሆነው ወገን ተጐጂው ያወጣውን ሙሉ ወጭ እንዲተካለት ሊወሰን ይችላል::

### II. በምትክ ስለመካስ (Exchange Value)

በተጐጂው ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት የንብረቱ ዋጋ እንዲቀንስ የተደረገ ከሆነ ለጉዳቱ ሐላፊ የሆነው ወገን ልዩነቱን እንዲከፍል በማድረግ የመካስ መንገድ ነው:: በዚህ ሥልት ካሳ ለማስከፍል የንብረቱን ከጉዳቱ በፊት የነበረውን የገበያ ዋጋ ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በሌላ ሁኔታ ደግሞ በጉዳቱ ምክንያት ዋጋው እንዲቀንስ የሆነው የንብረቱ የኪራይ ዋጋ ከሆነ ይኸው ከግንዛቤ ተወስዶ ካሳውን ማስላት ያስፈልጋል:: ለሁለተኛው ሁኔታ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው በመሬት ይዞታ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው:: በኢትዮጵያ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ በመሆኑ ለመሬት የገበያ ዋጋ የለውም:: ስለሆነም የመሬት ይዞታ ማከራየት ስለሚቻል ይኸው የኪራይ ዋጋ ካሳውን ለማስላት መሠረት ይሆናል::

### III. ሊገኝ ይችል የነበረው ጥቅም በማመዛዘን ስለመካስ (Utility Value)

በተጐጂው ላይ የደረሰው ጉዳት ትርፍ ወይም ጥቅም በማግኘት መብት ላይ ሲሆን ለምሳሌ:- በንግድ ሥራ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ምክንያት የደረስ ጉዳት ከሆነ ተጐጂው ያጣው ትርፍ ተመዛዝኖ ካሳ እንዲከፈለው ይወሰናል::

# ለአካል ጉዳት እና ለሞት አደጋ ካሳ አከፋፈል

የተመዛዘነ (የተመጣጠነ) የካሳ አከፋፈል ሥርዓትን በሚመለከት በአካል ጉዳት እና በሞት አደጋ የካሳ አከፋፈልን ማየቱ ከተጨባጭ ሁኔታዎች አንፃር ተገቢ ስለሚሆን እንደሚከተለው ቀርቧል::

## I. ለአካል ጉዳት ካሳ አከፋፈል

በሰው አካል ላይ ለሚደርስ ጉዳት ተመጣጣኝ ካሳ ማስላት እጅግ አስቸጋሪ ነው:: የሰው ልጅ አካል በገበያ ዋጋ የሚተመን ባለመሆኑ በአንድ ሰው አካል ላይ የሚደርሰውን ጉዳት በገንዘብ አስልቶ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ወይም የማይቻል ይሆናል:: የሆነ ሆነ በሰው ልጅ በአንድ የአካል ክፍል ወይም ክፍሎች ጉዳት በደረሰ ጊዜ ሊከፈለው የሚችለውን ካሳ ለመወሰን ጉዳት የደረሰበት የአካል ክፍል ለተጐጂው ገቢ ማግኘት ያለው ጠቀሜታ ከግንዛቤ በማስገባት በአካሉ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ያወጣውን ወይም ወደፊት ሊያጣው

የሚችለውን ገቢ (ጥቅም) በማስላት ለጉዳቱ ሐላፊ የሆነው ወገን ለተጐጂው ካሳ እንዲከፍለው ሊወሰን ይችላል።

አካሉ ለተጎደ ሰው ካሳን ለመወሳን ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

- የጉዳቱ አይነትና ደረጃ (ሙሉና ቋሚ፣ ከፍልና ቋሚ፣ ጊዜያዊ የአካል ጉዳት መሆኑ)
- የተጎደው የአካል ክፍል ከተጎጂው የመስራት አቅምና ከስራው ጋር ያለው ግንኙነት
- ተጎጂው ከጉዳቱ በፊት ይሰራ የነበራው ወይም ተስማርቶበት የነበረ ስራ (በደመወዝ የሚሰራ ሰራተኛ፣ የራሱን ስራ እየሰራ የሚኖር ስራ የማይሰራ ወይም ስራ የሌለው ስለመሆኑ)
- የተጎደው የአካል ክፍል (አይን እጅ እግር)
- የተጎጂው የአሁንና የወደፊት እድሜ ናቸው

እነዚህን ነጥቦች መሰረት በማድረግ የጉዳት ካሳ ሲወሰን ለተመሳሳይ የአካል ጉዳት ራሱ የተለያየ የካሳ ልክ ሊወሰን የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል። ሆኖም እንዲህ አይነቱ የጉዳት ካሳ በሚሰላበት ጊዜ የጉዳትና ካሳ ተመጣጣኝነት አጠቃላይ ደንብን ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት መደረግ አለበት።

## 1. የተቀጣሪ ሠራተኛ አካል ጉዳት:-

አንድ ተቀጥሮ የሚስራ ሠራተኛ በአካሉ ላይ ጉዳት ከደረሰበት በጉዳቱ ምክንያት የሚያጣው ጥቅም ሊኖር ይችላል። ጉዳቱ የደረሰበት ተቀጥሮ ከሚሰራው ሥራ ጋር የተገናኘ በሆነ ጊዜ ማለትም በሥራው ምክንያት የደረሰ የአካል ጉዳት ከሆነ ስለ ካሳ አከፋፈሉም ሁኔታ ከአሰሪና ሠራተኛ ሕግ አንፃር የሚታይ ይሆናል። ነገር ግን የደረሰበት ጉዳት ከሥራው ጋር በማይገናኝ መልኩ ከሆነ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ሐላፊነት በሚመለከተው ሕግ መሠረት የሚሸፈን ይሆናል።

በተቀጣሪ ሠራተኛ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ጊዜያዊ ጉዳት ከሆነ በጉዳቱ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ሥራ ባለመስራቱ ያጣው ገቢ ለጉዳት ካሳው ስሌት መሠረት ሆኖ ይኸው እንዲከፈለው ይወስናል።

በተቀጣሪ ሠራተኛ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ቋሚ የሆነና ከጉዳቱ በፊት ይስራ የነበረው ሥራ ለዘለቄታው መስራት የማይችል መሆኑ ከተረጋገጠ ግን ወደፊት የሚደርስ ጉዳት ተስልቶ የጉዳት ካሳ እንዲከፍለው ይወስንለታል። ቋሚ የሆነ

የአካል ጉዳት በደረሰ ጊዜ የወደፊት የጉዳት ካሳን ለመወሰን የሚከተሉትን መንገዶች (ስልቶች) መከተል ያስፈልጋል።

## ሀ. የደረሰውን የጉዳት መጠን ማገናዘብ:-

የደረሰበት የአካል ጉዳት የሠራተኛው የመሥራት ችሎት ሙሉ በሙሉ ሊያሳጣው ወይም በከፊል ሊያሳጣው ይችላል:: ይህም ማለት ጉዳቱ የደረሰበት የአካል ክፍል ሠራተኛው ይሰራ ከነበረው የሥራ ዓይነት (የሥራ ዘርፍ) አንፃር ያለው ጠቀሜታ ወሳኝ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም:: ለምሳሌ:- በእጅጣት ላይ የደረሰ ጉዳት ለአንድ የሕግ ጠበቃ ያለው ጠቀሜታ እና ለአንድ ታይፒስት ያለው ጠቃሜታ  ከፍተኛ ልዩነት ያለው ነው:: ለታይፒሲት እንደሙሉ ጉዳት ሊወሰድ የሚችል ሲሆን ለጠበቃው ግን ከፍል ጉዳት ብቻ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል:: የሕክምና ባለሞያዎች በሰው ልጅ አካል ላይ የደረሰን ጉዳት በተመለከተ ጉዳቱ የደረሰበትን የአካል ክፍል ከጠቅላላው አካሉ ያለውን ድርሻ በመቶኛ በማስላት ሞያዊ ማስረጃ ይሰጣሉ:: ለምሳሌ በአንድ የእጅ ጣት ላይ የደረሰ ጉዳት (የጣት መቆረጥ) ከጠቅላላው አካል አሥር በመቶ (10%) የሚል ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ይህ የሐኪም ማስረጃ ከተጐጂው ሞያ (ሥራ) አንፃር የሚያስከትለውን ጉዳት ወይም የመሥራት ችሎታ የሚገልፅ አይደለም:: ከላይ በተጠቀሰው ምሳሌ በታይፒሲት ላይ የደረሰ የእጅ ጣት መቆረጥ ጉዳት የታይፒሲቷን የወደፊት በታይፒሲትነት የመሥራት ችሎት መቶ በመቶ የቀነስ ነው ሊባል ይችላል::

## ለ. ጉዳቱ በደረሰ ጊዜ የሠራተኛው ገቢ ወይም ደሞዝ:-

በሠራተኛው ላይ  የደረሰው የአካል ጉዳት ሠራተኛውን ለተወሰነ ጊዜ ከሥራ ያስተጓጉለው ከሆነም ወይም ሙሉ በሙሉ (ለወደፊቱ) ሥራውን ከመሰራት ያስተጓጉለው ከሆነም ጉዳቱን ለማስላት በጉዳቱ ወቅት ያገኝ የነበረው ገቢ (ደሞዝ) የጉዳት ካሳውን ለማስላት መሠረት ይሆናል::

## ሐ. የሠራተኛው በሥራ ላይ የሚቆይበት እድሜ:-

ወደፊት የሚደርስ ጉዳትን ለማስላት በጉዳቱ ወቅት ሠራተኛው ያለው እድሜ መሠረት በማድረግ ወደፊት በሥራ ላይ የሚቆይበት ቀሪ እድሜ ከግምት መወሰድ ይኖርበታል::

## 2. የራሱን ሥራ በመስራት የሚተዳደር ሰው:- (Self –Employed)

ተቀጥሮ ሳይሆን የራሱን የሆነን ሥራ በመስራት የሚተዳደር ሰው ላይ የአካል ጉዳት በደረሰበት ጊዜ የጉዳት ካሳውን ማስላት ከተቀጣሪ ሠራተኛ አንፃር ሊከብድ ይችላል::

ስለሆነም የግለሰቡን የዓመት ገቢ ለመንግስት ከሚከፍለው ግብር ወይም በሌላ ሁኔታ በማጣራት የዓመት ገቢውን መሠረት በማድረግ እንደ ጉዳቱ ዓይነት ካሳውን ማስላት ያስፈልጋል::

### 3. ሥራ በመስራት ላይ ያልነበረ ሰው ላይ የደረሰ የአካል ጉዳት

አንድ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ ላይሰራ ይችላል፣ ለመሥራት ባለመፈለግ፣ የሚመጥን ሥራ ባለማግኘት ወይም አልፎ አልፎ ብቻ በሥራ ላይ የመቆየት እና ሌላም ሊጠቀስ ይችላል:: በእንደዚህ ዓይነት ሰው ላይ በአካሉ ጉዳት በመድረሱ ያጣው ገቢ ወይም ወደፊት ሊያጣው የሚችለውን ገቢ ለማስላት መሠረት ሊሆን የሚችል ተጨባጭ ነገር ማግኘት ያስቸግራል:: ስለሆነም በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ.2102 መሠረት ርትዕን መሠረት በማድረግ ዳኞች ምክንያታዊ የሆነ የጉዳት ካሳ ለተጐጂው እንዲከፈለው ሊወስኑ ይችላል::

## II. የሞት አደጋ (Mortal Accidents)

አንድ ሰው በደረሰበት አደጋ ምክንያት ሕይወቱን ሊያጣ ይችላል:: በአንድ ሰው የሞት አደጋ ሲደርስ ካሳ የሚከፍለው ለማን ነው? ካሳው እንዴት ይስላል የሚሉትን ነጥቦች በዋናነት በማንሳት እንመለከታለን::

- በሞት አደጋ ካሳ የሚከፍላቸው በፍ/ብሔር ሕግ ቁ.2095 እንደተመለከተው በሞት አደጋ ካሳ እንዲከፈላቸው የመጠየቅ መብት ያላቸው የሟቹ ባል ወይም ሚስት ወላጆቹና ልጆቹ ናቸው:: ካሳውን የሚጠይቁት በራሳቸው ስም ሲሆን ይኸውም በመተዳደሪያ ረገድ ለሚደርስባቸው ጉዳት ነው::

- ለሞት አደጋው ሐላፊ የሆነው ወገን የሚከፍለው የካሳ ዓይነት ለምግብ

ወይም መተዳደሪያ እንደሚከፈለው ጡረታ መልክ እና ዓይነት እንደሆነም

በአንቀፅ ተመልክቷል::

- በሞት አደጋ ካሳ የመጠየቅ መብት የተሰጣቸው ሰዎች ሌላ ቀለብ

እንዲሰጣቸው የሚጠይቁት ዘመዶች ቢኖራቸውን እንኳ በሞት አደጋው

ምክንያት የሚገባቸው ካሳ የማግኘት መብት እንዳላቸው ተመልክቷል::

- በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ.2095 (2) ላይ የተመለከተው በሞት አደጋ የሚከፈል ካሳ መልክ እና ዓይነቱ ለመተዳደሪያ እንደሚከፈል የጡረታ አከፋፈል መሆን እንዳለበት ተደንግጓል:: ስለሆነም ፍ/ቤት በሞት አደጋ ምክንያት የሚከፈለውን ካሳ ለመውስን በፍ/ብ/ሕግ በተለይም የቤተሰብ ሕግ ላይ ወይም በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ ላይ የተመለከተውን የቀለብ አወሳስን ሥርዓት ማገናዘብ ይጠበቅበታል::

- በዚሁም መሠረት **በፍ/ብ/ሕግ ቁ.812** ወይም **በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ ቁ.201** ላይ እንደተመለከተው ቀለብ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ወገን ሠርቶ ለመብላት ወይም አስፈላጊ የሆነ ገቢ የማግኘት አቅም የሌለውና በችግር ላይ የወደቀ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም በሞት አደጋ ምክንያት ካሳ እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት ያለው ወገንም ይህንኑ የማሳየት ወይም የማስረዳት ግዴታ ይኖርታል፡፡

- እንደዚሁም **በፍ/ብሔር ሕግ ቁ.813** ወይም በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ **አንቀፅ 202** መሠረት የቀለብ ተቀባዩን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን የቀለብ ሰጪውን አቅም ማመዛዘን እንደሚያስፈልግ በሕጐቹ ላይ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም በሞት አደጋ ካሳ አከፋፈል ውሳኔ አሰጣጥ ላይም ይህንኑ መከተል ያስፈልጋል፡፡

⇨ በመሠረቱ የቀለብ አከፋፈል ሥርዓት በአንድ ጊዜ የተወሰነ ገንዘብ (Lump Sum) በመክፈል የሚፈፀም ሳይሆን በየወቅቱ (Periodic) መሆኑን በፍትሐ ብሔርም ሆነ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የክፍያው መጠን የመጨመር፣ የመቀነስ ወይም ክፍያው እንዲቋረጥ ሊወሰን እንደሚችል በቤተሰብ ሕጐች ላይ ተመልክቷል፡፡

⇨ ሌላው ሊታለፍ የማይገባው መሠረታዊ ነጥብ **በፍ/ብሔር ሕጉ ቁ.2096** ላይ የተደነገገው ነው፡፡ በሞት አደጋ ምክንያት ካሳ የመጠየቅ መብት ያላቸው **በቁ.2095 የተጠቀሱት** ብቻ ናቸው፡፡ ሌሎች ሰዎች ምንም እንኳ ሟቹ ይረዳቸው ወይም ያስተዳድራቸው የነበረ ቢሆንም ካሳ የመጠየቅ መብት እንደሌላቸው በግልፅ ተደንግገኋል፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በሞት

አደጋ ምክንያት ካሳ የመጠየቅ መብት የተሰጣቸው በፍ/ብሔር ሕግ ቁ.2095 ላይ የተጠቀሱት ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በሞት አደጋ ምክንያት የሚከፈል ካሳ ለሌሎች አደጋዎች ወይም ጉዳቶች ከሚከፈል የካሳ አከፋፈል ሥርዓት የተለየ በመሆኑ ከውል ውጪ ስለሚደርስ ሐላፊነት የሚመለከቱ የሕግ ድንጋጌዎች ብቻን በማየት ለመፈፀም ስለማይቻል ተዛማጅ ሕጐችን በጥንቃቄ ማየትና መረዳትን ይጠይቃል፡፡

## 4.1.2. የማይመጣጠን (Non-Equivalence) የካሳ አከፋፈል ሥርዓት

ይህ የካሳ (ኪሳራ) አከፋፈል ሥርዓት በሕጉ በቁ.2091 ላይ ለተደነገገው ማለትም «... በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን አለበት» ለሚለው አጠቃላይ መርሕ የተለየ (Exception) ሁኔታዎች የሚያካትት የካሳ አከፋፈል ሥርዓት ነው::

የማይመጣጠን የካሳ አከፋፈል ሥርዓትን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ ይቻላል:: ይኸውም የተበዳዩ ጥፋት (የፍ/ብሔር ሕግ 2098) እና ርትዕ (Equity) ናቸው::

I. **የተበዳዩ ጥፋት**

የተበዳይ ጥፋት ወይም የካሳ ጠያቂው ጥፋት የሚወሰነውን የካሳ መጠን ለመቀነስ (እንዲቀንስ) ምክንያት ይሆናል:: ይህም ማለት ተጐጂው ለደረሰበት ጉዳት የራሱ አስተዋፆ ያለበት ከሆነ ሊከፈለው የሚችለውን ካሳ ከደረሰበት ጉዳት ጋር የተመጣጠን ሳይሆን የቀነስ ይሆናል::

የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ.2098 ድንጋጌን ስንመለከት ተበዳዩ ላይ የደረሰው ጉዳት የራሱ የተበዳዩ ከፊል ጥፋት አስተዋጾ ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ ከሆነ ለተበዳዩ የሚከፈለው ካሳም በከፍል እንደሚሆን በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ ተመልክቷል:: ስለሆነም በክፍል ካሳውን ለመወስን የአካባቢ ሁኔታዎችን መሠረት ማድረግ በተለይም የተበዳዩን አስትዋፆ መጠን (የጥፋት መጠን) በማመዛዘን ጉዳቱን አደረሰ የተባለው ሰው በመደበኛ ሁኔታዎች ሊከፍለው የሚችለው የካሳ መጠን በመቀነስ ሊወስን እንደሚገባ የፍ/ብሔር ቁ.2098 (2) ያመለክታል::

## II. ርትዕን መሠረት በማድረግ ካሳ የሚወስንበት ልዩ ሁኔታ

በርትዕ ውሳኔ መስጠት ማለት በሕግ ላይ የተቀመጡትን ሁኔታዎች በአግባቡ መከተል ሳያስፈልግ ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ያለ አድልዎ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚሰጥ ውሳኔ እንደማለት ሲሆን ሕግን ያልተከተለ ፍትህ (Justice without law) በሚል አባባል የሚገለፅ ሥርዓት ነው ለማለት ይቻላል::

በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ርትዕን መሠረት በማድረግ አንድ ለደረስ ጉዳት የሚከፈለውን ካሳ (ኪሳራ) መወሰን የሚቻለው በሕጉ የተቀመጡ ሁኔታዎች

ሲያጋጥሙ ነው፡፡ ስለሆነም ዳኞች በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ ለደረሰው ጉዳት ሐላፊ የሆነው ወገን የሚከፈለው ካሳ ከደረሰው የጉዳት መጠን ያነሰ ካሳ እንዲከፈል ለመወሰን ይችላሉ፡፡ ርትዕን መሠረት በማድረግ ካሳ የሚወሰንበትን ሁኔታዎች ቀጥለን እንመልከት፡፡

## ሀ. ድርጊቱ ጥፋት መሆኑን ባለማወቅ የደረሰ ጉዳት :- (ቁ.2099)

በፍ/ብሔር ሕግ ቁ.2099 ላይ እንደተመለከተው የሥራውን (የድርጊቱን) ጥፋት ለመገመት የማይችል ሰው ሐላፊነት የሚያስከትል ድርጊት ፈፅሞ የተገኘ እንደሆነ አጥፊው ሊከፍል የሚገባውን የካሳ ልክ ዳኞች በርትዕ ለመወስን እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ ይህ ሁኔታ ሊያጋጥም የሚችለው ሕፃን ልጅ ወይም አካለ መጠን ያላደረስ ልጅ የሚፈፅመው ድርጊት ወይም አእምሮው የጉደለ ሰው የሚፅመው ድርጊት ሀላፊነትን የሚያመጣ በሆነ ጊዜ ለተጉጂው የሚከፈለውን የካሳ መጠን ዳኞች ከደረሰው ጉዳት በማሳነስ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

ይህ ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ዳኞች ርትዕን መሠረት በማድረግ ሲወስኑ የተጉጂውና በሐላፊነት የሚጠየቀውን ወገን የሐብት መጠን ማመዛዘን እንደዚሁም በሐላፊነት የሚጠየቀውን ወገን ካሳ በመክፈሉ ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት ማመዛዘን እንደሚገባቸው **የፍ/ብሔር ቁ.** 2099 (2) ያመለክታል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>:- ጉዳት የደረሰበት ወገን ታዋቂ ነጋዴና በርካታ ሐብትና ንብረት ያለው ቢሆን በሌላ በኩል ደግሞ ካሳ የመክፈል ግዴታ ያለበት ወገን በቀን ሥራ የሚተዳደርና አነስተኛ ገቢ ያለው የብዙ ቤተሰብ አስተዳደሪ ከሆነ ወይም በተቃራኒም ምሳሌውን ብናስቀምጠው ርትዕን መሠረት በማድረግ የሚወሰነው ካሳ በሁለቱም ሁኔታዎች የተለያዩ የካሳ መጠን (ልክ) መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

## ለ. በበላይ ትዕዛዝ ምክንያት የሚፈፀም ጥፋት (ቁ.2100)

የበታች ሠራተኛ የበላይ አለቃውን ሕጋዊ ያልሆነ ወይም ሕገ ወጥ ትዕዛዝ የፈፀመ እንደሆነ የበታች ሠራተኛ ለፈፀመው ሕገ ወጥ ድርጊት ሀላፊ ነው፡፡ ሆኖም የበታች ሠራተኛ በዲሲኘሊን ወይም በታዛዥነት ተገቢ ስሜት የበላይ አለቃውን ሕጋዊ ያልሆነ ትዕዛዝ በመፈፀሙ ምክንያት በሌላ ሰው ላይ ለደረሰው ጉዳት የሚከፍለው ካሳ ሊቀንስለት ይችላል፡፡ የበታች ሠራተኛ በበላይ አለቃ ትዕዛዝ ምክንያት ለፈፀመው ጥፋት ለተጉጂው የሚከፍለውን ካሳ ለመቀነስ ዳኞች የመታዘዙን ተገቢነት ማነስ ማደጉን ማመዛዘን እንዳለባቸው **በፍ/ብ/ሕግ ቁ.2100** ተደንግጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

በበላይ ትዕዛዝ ምክንያት የበታች ሠራተኛ የሚፈፅመው የጥፋት ድርጊትን በተመለከተ ስለ የበላይ ትዕዛዝ **በፍ/ብሔር ሕግ ቁ.2036** የተደነገገውን መሠረታዊ መርሕ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በፍ/ብሔር ቁ.2036 ላይ የተመለከተው በበላይ አለቃ እና በበታች ሠራተኛ መካከል ያለው ግንኙነት መንግስታዊ (Public Relstionship) ማለትም በአሰተዳደራዊ መስሪያ ቤቶች ወይም በወታደራዊ ተቋማት ያለውን የበላይና የበታች ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ የበታች ሠራተኛ የበላይ አለቃውን ትዕዛዝ ሕገ ወጥነት እየተረዳ በተለይም ትዕዛዙን የሰጠው የበላይ አለቃ ትዕዛዙን የመስጠት ሥልጣን ወይም ችሎት የሌለውና ትዕዛዙም ሕገ ወጥ የወንጀል ተግባር መሆኑን እያወቀ ይህን ትዕዛዝ የፈፀመ የበታች ሠራተኛ ጥፋተኛ መሆኑ በሕጉ ተደንግጓል፡፡

ሆኖም ግን የበታች ሠራተኛ በበላይ አለቃው እንዲፈፅም የታዘዘውን ድርጊት ሕገ ወጥነት ያወቀ ቢሆንም በአስተዳደራዊ (መንግስታዊ) ወይም በወታደራዊ ዲሲኘሊን ምክንያት ስለተሰጠው ትዕዛዝ ከበላይ አለቃው ጋር ለመወያየት ወይም ለመከራከር የማይችል ከሆነ፣ ወይም የበታች ሠራተኛ

ከታዘዘው ውጭ ሌላ ነገር ለማድረግ በማይችልበት ሁኔታ ውሰጥ በመሆኑ የበላይ አለቃውን ሕገ ወጥ ትዕዛዝ የፈፀመ ከሆነ ለድርጊቱ ጥፋተኛ አይባልም፡፡ <u>ለምሳሌ፡-</u> የበታች ሠራተኛ ሕገ ወጥ ድርጊት እንዲፈፅም ሲታዘዝ በመሳሪያ ተገዶ እንደሆነ (At gun point) ወይም የታዘዘውን ባይፈፅም ከሥራው እንደሚባረር ጥብቅ ትዕዛዝ የተሰጠው ከሆነ በፍ/ብሔር ሕግ ቁ. 2036 መሠረት የበታች ሰራተኛ ለተፈፀመው ድርጊት ጥፋተኛ ሊሆን እንደማይገባ መረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም **በፍ/ብሔር ሕገ ቁ. 2100** መሠረት የበታች ሠራተኛ የበላይ አለቃውን ሕገ ወጥ ትዕዛዝ በመከተል ጥፋት ፈፅሞ ከተገኘ የበታች ሠራተኛ ለተጐጂው የሚከፈለውን ካሳ ለመቀነስ በትዕዛዝ ሰጪውና ተቀባይ መካከል የነበረው ሁኔታዎች እና የበታች ሠራተኛውን ሐሳብ (Motives) በሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## ሐ. <u>ይደርሳል ተብሎ ሊታስብ የማይችል ጉዳት ቁ.2101</u>

በመሠረቱ ለአንድ የደረሰ ጉዳት መከፈል ያለበት ካሳ ከጉዳቱ ጋር ተመዛዛኝ (ተመጣጣኝ) መሆን እንደሚገባ ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም ግን በእያንዳንዱ ሁኔታዎች የተለየ ነገር ሊያጋጥም ይችላል፡፡ <u>ለምሳሌ</u>፡- አንድ ለደረሰ ጉዳት በተለመዱ ሁኔታዎች 1000 (አንድ ሺህ ብር) ካሳ የሚያስከፍል ቢሆንም ሊታሰብ በማይችል አጋጣሚ ሁኔታዎች ምክንያት በእርግጥ የደረሰው ጉዳት 10.000 (አሥር ሺህ ብር) ሆኖ ከተገኘ ዳኞች ርትዕን መሠረት በማድረግ ለተጐጂው የሚከፈለውን ካሳ መቀነስ

እንደሚችሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.2101 (1) ላይ ተደንግጓል:: ይህን ሁኔታ በምሳሌ ማስደገፍ ነገሩን ይበልጥ ግልፅ ስለሚያደርገው የሚከተለውን ምሳሌ:- እንመልከት::

✷ ለምሳሌ:- አንድ የመኪና አሽከሪካሪ መኪናውን መቆም በተፈቀደ ቦታ አግባቡ አቁሞ ሞተሩን ካጠፋ ብኃላ በሩን ከፍቶ ለመውረድ ሲል ከጐኑ በኩል እየመጣ የነበረው እግረኛ ባለማስተዋሉ የመኪናውን በር ሲከፍት እግረኛው የመኪናው በር አጠገብ ደርሶ ስለነበር የመኪናው በር ሲከፈት እግረኛው በእጁ ያደረገው ሰዓት (የእጅ ሰዓት) በመኪናው በር ተመቶ ሰዓቱ ተሰብሮ ከጥቅም ውጭ ቢሆን፣ እንበልና በአካባቢው አንድ የእጅ ሰዓት በጣም ውድ የሚባለው 500 (አምስት መቶ ብር) ቢሆን፣ ሰዓቱ

ለተሰበረበት ተጐጂ ሊከፈለው የሚገባው ካሳ (ኪሳራ) እስከ 500 ብር ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል:: ሆኖም ግን ይህ የተሰበረው የእጅ ሰዓት ለተጐጂው ከውጭ ሐገር የተላከለትና በልዩ ትዕዛዝ የተሰራዋጋውም እስከ 5000 (አምስት ሺህ ብር) የሚገመት ነው::

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ለተጐጂው የሚከፈለው ካሳ በደረሰበት ጉዳት ልክ መሆን ይገባዋል ከተባለ ውሳኔው ፍትሐዊነት የጐደለው ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም ካሳ የመክፈል ግዴታ ያለበትን እና የተጐጂውን ሁኔታ በማገናዘብ ርትዕን መሠረት በማድረግ ለተጐጂው የሚከፈለው ካሳ መቀነስ ተገቢ ይሆናል::

በፍ/ብሔር ቁ.2101 መሠረት በርትዕ የካሳ መጠንን መቀነስ ሆነ ተብሎ ለተደረገ የጥፋት ድርጊት ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን የፍ/ብሔር ሕግ ቁ.2101 (2) ያመለክታል::

## መ. ስለ ግምት አስቸጋሪነት (ቁ.21020

ጉዳት ስለመድረሱ የተረጋገጠ ሲሆን ለተጐጂው ተመዛዛኝ (ተመጣጣኝ) ካሳ እንዲከፈለው መወሰን የሚያከራክር አይሆንም:: ሆኖም ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች በተጐጂው ላይ ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ ሆኖ የጉዳቱን መጠን ማስላት ግን እጅግ በጣም አስቸጋሪ ወይም የጉዳቱን መጠን ማስላት የማይቻልበት ሁኔታ ያጋጥማል:: እንደዚህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም ዳኞች የነገሮቹን ተራ ሁኔታዎች እና ተጐጂው ያደረገውን ጥንቃቄ በማመዛዘን የጉዳቱን መጠን በመገመት በርትዕ የጉዳት ካሳውን ዳኞች መወሰን እንዳለባቸው የፍ/ብሔር ሕግ ቁ. 2102 (1) ይደነግጋል::

- ነገሩን በምሳሌ:- እንመልከት:-

✴ምሳሌ፡- አብደላ የተባለ ግለሰብ በግብርና ሥራ የሚተዳደር ሲሆን ሥራውን በራሱ ጉልበት በመሥራት በዓመት እስከ 20 ኩንታል የተለያዩ ሰብሎችን በማምረት ለቤተሰብ የሚሆን ቀለብ በማስተረፋ ቀሪውን ለገበያ በማቅረብ እስከ 7000 (ሰባት ሺህ ብር) ገቢ እንደሚያገኝ ይታወቃል፡፡ አብደላ በዚህ ሁኔታ ሕይወቱን የሚመራ ገበሬ ነው እንደዚሁም መንግስት በዘረጋው የሰብል ምርት ኤክስቴንሽን ኘሮግራም ለመታቀፍ በዝግጅት ላይ እያለ የአካባቢው ነዋሪ ከሆነው አደም የሚባል ግለሰብ ጋር በተፈጠረ አለመግባባት አደም አብደላን በዱላ በመደብደብ የአካል ጉዳት

ያደረሰበት ሲሆን በዚህም ምክንያት አብደላ ለሁለት ወራት ከሥራ የተሰተጓጉለ ሲሆን በኤክስቴንሽን ኘሮግራም ለመታቀፍ ያደረገው ዝግጅት በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ እንደዚሁም አብደላ ከደረሰበት ጉዳት ታክሞ ከሕመሙ አገግሞ ወደ ሥራው ቢመለስም አልፎ አልፎ ግን የግብርና ሥራውን እንደቀድሞው ለመሥራት ስለማይችል የቀን ሠራተኛ በመቅጠር ያሰራል፡፡

ስለሆነም አብደላ በኤክስቴንሽን ኘሮግራም በመታቀፍ ምርቱና ገቢውን ለማሳደግ ያቀደው ሳይሳካ መቅረቱ የተረጋገጠ ቢሆንም በእርግጠኝነት ግን በኤክስቴንሽን የመታቀፍ እድሉ በመጨናገፍ ያጣው ገቢ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ አይቻልም፡፡ እንደዚሁም እንደቀድሞው ሥራው መሥራት በማይችልበት ወቅት የቀን ሠራተኛ በመቅጠር ማስራቱ የተረጋገጠ ቢሆንም በዓመት ወይም በወር ለምን ያህል ጊዜ የቀን ሠራተኛ በመቅጠር ሊያስራ እንደሚችል በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም፡፡ ስለሆነም ሥራው ለመሥራት የሚያወጣውን ተጨማሪ ወጪ በእርግጠኝነት ማወቅ አይቻልም፡፡

እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በእርግጠኝነት ካሳውን ማስላት አስቸጋሪ ወይም የማይቻል ይሆናል፡፡ ስለሆነም በአካባቢው ሁኔታዎች በመነሳት አንድ አንዴ አብደላ ያለ ገበያ በአክስቴንሽን ቢታቀፍ ከቀድሞው ምርቱና ገቢው አንፃር ሊያገኝ የሚችለውን ተጨማሪ ገቢ በመገመት የካሳ መጠነን በርትዕ መወሰን ተገቢ ይሆናል፡፡ ለቀን ሠራተኛ የሚያወጣውንም ተጨማሪ ወጭ በአንድ ወር ውስጥ ለሶስት ወይም ለአምስት ቀን የቀን ሠራተኛ ሊቀጥር ይችላል፡፡ በሚል ግምት በመነሳት ለቀን ሠራተኛ የሚከፈለውን የአካባቢ ልምድ መሠረት በማድረግ በግምት ርትዕን መሠረት በማድረግ የካሳውን መጠን ማስላት ተገቢ ይሆናል፡፡

✴በፍ/ብሔር ሕግ ቁ.2102 መሠረት በርትዕ ካሳን መወሰን ለዳኞች የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ (Mandatory) መሆኑን ከሕጉ እንገነዘባለን፡፡ ሌላው በዚህ ድንጋጌ የምንረዳው እንደሌሎቹ ድንጋጌዎች የካሳ መጠንን ቀንሶ የመወሰን ነገር ሳይሆን

ካሳውን በእርግጠኝነት ማስላት ባልተቻለበት ሁኔታ የሚወሰድ አማራጭ የካሳ አወሳሰን መንገድ መሆኑን መገንዘብ

ያስፈልጋል፡፡

## ሠ. አስፈላጊ ሁኔታ (Necessity) (ቁ.2103)

አንድ ሰው በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰው በጥፋት አድርጐት ሳይሆን ራሱን ለማዳን ወይም ሌላው ሰው ከጉዳት ወይም ከድንገተኛ አደጋ ለማዳን ሲል ጉዳት አድርሶ ከሆነ በዚህ ምክኒያት በንብረቱ ላይ ጉዳት ለደረሰበት ተጎጂ የሚከፈለው ካሳ ከጉዳቱ ጋር ተመዛዝኖ ሳይሆን በርትዕ መሆን እንደሚገባው የፍ/ብሔር ሕግ ቁ. 2103 ይደነግጋል፡፡

ስለሆነም በዚህ ድንጋጌ ርትዕን መሰረት በማድረግ መወሰን ለዳኞች ምርጫ የተሰጠ ሳይሆን ግዴታ (Mandatiry) ነው፡፡ በመሆኑም በተጐጂው ላይ ከደረሰው የጉዳት ልክ ያነሰ ካሳ እንዲከፈል የሚወስን ይሆናል፡፡

## ረ. የተቀጣሪ ሠራተኛ ሐላፊነት

በፍ/ብሔር ሕግ ከቁ.2157-2159 የተመለከቱት ሁኔታዎች የመንግሥት ሠራተኛ፣ የግል ድርጅት ሠራተኛ ወይም በሌላ ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ ሥራው በሚሰራበት ጊዜ ጥፋት ከፈፀመና በጥፋቱም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት አድርሶ ከሆነ ሠራተኛው ለተጎጂው የሚከፍለውን ካሳ በሙሉ ወይም በከፊል ቀጣሪው ድርጅት ወይም ሰው እንዲከፍል ዳኞች ሊወስኑ እንደሚችሉ በፍ/ብሔር ሕግ ቁ. 2157 (1) ላይ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም አንድ ተቀጣሪ ሠራተኛ ሥራውን በሚሰራበት ወቅት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት አድርሶ ከሆነ የሰራተኛውን የጥፋት ድርጊት ከባድነት ደረጃ እና ሠራተኛው የጥፋት ድርጊቱን የፈፀመው ከተሰጠው ስራ አብልጦ በመስራቱ ምክንያት መሆን አለመሆኑን በማመዛዘን ሰራተኛውን ከካሳ ክፍያ ሙሉ በሙሉ ነፃ ማድረግ ወይም ከፍሉን ብቻ እንዲከፍል መወሰን እንደሚገባ በፍ/ብሔር ቁ. 2157 (2) ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሆኖም ግን ሠራተኛው ሐላፊነት ያመጣበትን የጥፋት ድርጊት የፈፀመው አስቦ ከሆነ ወይም በፈፀመው የጥፋት ድርጊት በወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ከሆነ በካሳ አከፋፈሉም ላይ ሙሉ ሐላፊ እንደሚሆን የፍ/ብሔር ሕግ ቁ. 2159 ያስገነዝበናል፡፡

በአጠቃላይ ተቀጣሪ ሰራተኛ በስራው ምክንያት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት አድርሶ ከሆነ በሕጉ አግባብ ከካሳ ክፍያ ሙሉ በሙሉ ነፃ የመሆን ወይም በከፍል ብቻ ሐላፊ የመሆን እድሉ ያለው መሆኑና ይህም በሕጉ ለዳኞች በተሰጠው በርትዕ የመወሰን ስልጣን መሠረት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.2. ለሕሊና ጉዳት የካሳ አከፋፈል ሥርዓት (Modes and Extent of Compensation for Moral Damage)

አንድ ተጎጂ በደረሰበት ጉዳት በገንዘብ ረገድ ወይም በገንዘብ ሊገመት የሚችል ጉዳት ባይደርስበትም፣ ለደረሰበት የሕሊና ጉዳት ማለት ለደረሰበት ሐዘን፣ ብስጭት፣ ሐፍረት ወይም የስሜት መጎዳት ካሳ ሊከፈለው እንደሚቻል በፍ/ብሔር ሕግ ቁ. 2105 ላይ ተመልክቷል፡፡

በመሰረቱ የሕሊና ጉዳትን በገንዘብ ገምቶ መካስ የማይቻል ነው ምክንያቱም የሕሊና ጉዳት የሰው ልጅ የውስጥ ስሜት መጎዳት ስለሆነ ይህን የስሜት መጎዳት መለካት ወይም መገመት የማይቻል በመሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ በአንድ ሰው ላይ በደረሰበት ጉዳት የተሰማውን ሐዘን በስንት ብር ይገመታል ብለን ብንጠይቅ መልስ አናገኝለትም የሆነ ሆነ በሕጉ በግልፅ በተመለከተ ጊዜ ምንም

እንኳን ተመጣጣኝ ወይም ተመዛዛኝ ነው ባይባልም ለሕሊና ጉዳት የገንዘብ ካሳ እንደሚከፈል **በፍ/ብ/ሕግ ቁ.** 2105 (2) ላይ ተገልፃል፡፡

ስለዚህም በፍ/ብሔር ሕግ ቁ. 2105 ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው

1ኛ:- ለሕሊና ጉዳት የገንዘብ ካሳ የሚከፈለው በሕጉ ለተመለከቱ የጉዳት

ዓይነቶች ብቻ ነው መባሉ ለሕሊና ጉዳት የገንዘብ ካሳ መክፈል ልዩ

ሁኔታ እንጂ አጠቃላይ ድንጋጌ ያለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

2ኛ. የሕሊና ጉዳት ካሳ በገንዘብ ብቻ የሚከፈል ሳይሆን በሌሎች አማራጮች

ማለትም ከገንዘብ ክፍያ ውጪ ባሉት እንደ አጥፊው ተጎጂውን ይቅርታ

እንዲጠይቅ በማድረግ ዓይነት የሕሊና ጉዳትን ለመካስ እንደሚቻል

መገንዘብ ይቻላል፡፡

በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2105 /1/ ላይ እንደተመለከተው የሕሊና ጉዳት ካሣ የሚያስከፍለው በጥፋት ለተፈጸመ ጉዳት ነው፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2106 እስከ 2115 የሕሊና ጉዳት ካሣ ያስከፍላሉ ተብሎ የተደነገጉ ጉዳዮች ሁሉ በጥፋት የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ጥፋት ላይ በተመሠረተ ጉዳት እንጂ ጥፋት ሳይኖር የሚደርስ የሕሊና ጉዳት ካሣን አያስከፍልም፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍትሐ ብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 480/88 ላይ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የአንድ መኪና ባለቤት ጥፋት ሳይኖርበት የንብረቱ ባለቤት በመሆኑ ብቻ ኃላፊነት አለበት ብሎ ሕጉ በመወሰኑ ብቻ እንጂ ጥፋት በመፈጸሙ ምክንያት ስላልሆነ የሕሊና ጉዳት ካሣን ለመክፈል አይገደድም ብሎ ወስኗል፡፡

- በኢትዮጵያ የፍ/ብሔር ሕግ መሠረት ለተጎጂ የሚከፈለው የሕሊና ጉዳት ካሳ ከ1000 (አንድ ሺ ብር) መብለጥ እንደሌለበት **በፍ/ብሔር ሕግ ቁ.** 2116 (3) ላይ ተደንግጓል፡፡

- ለሕሊና ጉዳት የሚከፈለው የገንዘብ ካሳ የሚወሰነው ርትዕን መሠረት በማድረግ መሆኑ በፍ/ብሔር ሕግ ከቁ. 2106-2115 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.3. በሌላ አኳኋን የመካስ ሥርዓት

ለተጎጂ የሚከፈል የካሳ ልክ የሚወሰነው የደረሰበትን ጉዳት በማመዛዘን ከጉዳቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ እንዲከፈለው በመወሰን መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በሌላ በኩል በተጎጂው ላይ የደረሰውን ጉዳት በትክክል ለመገመት የማይቻል በሆነ ጊዜ በርትዕ የካሳውን ልክ መወሰን እንደሚቻልም ተመልክተናል፡፡

ተጎጂ ለደረሰበት ጉዳት የገንዘብ ካሳ እንዲያገኝ ከመወሰን ሌላም በሌሎች አማራጮች ጉዳቱን መካስ እንደሚቻል በፍ/ብሔር ሕግ ከቁ. 2118-2123 ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ እነዚህም፣

I. <u>የተወሰደውን ነገር (ዕቃ) ስለመመለስ (Restitution), ቁ.2118</u>

ከሕግ አግባብ ውጪ የተወሰደው ዕቃ ለባለመብቱ ወይም ለባለንብረቱ እንዲመለስ በመወሰን ንብረቱ ያለ አግባብ የተወሰደበት ተጎጂ እንዲካስ ማድረግ ይቻላል፡፡ ያለ አግባብ የተወሰደ ንብረት ለተጎጂው እንዲመለስ የሚወሰነው የተወሰደው ዕቃ ብቻ እንዲመለስ በሚል ሳይሆን ይህ የተወሰደው ዕቃ ያፈራቸው ጥቅሞችም ጭምር ለተጎጂው እንዲመለሱ በማድረግ ነው፡፡

ያለ አግባብ የወሰደውን ዕቃ እንዲመልስ የተወሰነበት ሰው ዕቃውን አጥፍቶት ከሆነ የዕቃውን ግምት መክፈል እንዳለበት በሕጉ ተመልክቷል፡፡ ዕቃውን እንዲመልስ የተወሰነበት ሰው ዕቃው ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ጠፍቶብኛል በማለት የሚያቀርበው መከላከያ ወይም ተቋውም ተቀባይነት የሌላው መሆኑም በሕጉ ተመልክቷል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>:- በተጉጂው ያለአግባብ የተወሰደበት ንብረት «ላም» ሲሆን ላሚ  በወሳጁ እጅ በቆየችበት ጊዜ ወልዳ ከሆነ ላሚ ለባላሐብቱ እንዲትመለስ ሲወሰን ከነ ጥጃው ጭምር ነው፡፡

ሆኖም ላሚን እንዲመልስ የተወሰነበት ሰው ላሚን ራሱ ዘንድ ባቆየበት ወቅት ለላሚ ምግብ እና ለመሳሰሉት ያወጣውን ወጪ የመጠየቅ መብት እንዳለው ማለትም ያለአግባብ ስለመበልፀግ በተመለከቱ ድንጋጌዎች መሠረት ባለላሙ (ተጉጂ) እንዲከፍለው መጠየቅ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁ.2118 ተደንግጓል፡፡

## II. **በአይነቱ ስለመተካት (Reparation) ቁ.2119**

የተጐጂው ንብረት የተበላሸ ወይም የተጐዳ ከሆነ ለጉዳቱ ሐላፊ የሆነ ሰው ባበላሸው ንብረት ምትክ ሌላ እንዲተካ ወይም በተባለው ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት የሚጠገን ወይም የሚታደስ ከሆነም ለጉዳቱ ሐላፊ የሆነው ሰው ሙሉ ወጪውን ከፍሉ ዕቃው እንዲጠገን ወይም እንዲታደስ እንዲያደርግ ይወሰንበታል፡፡

ሆኖም ተጐጂው የተበላሸበትን ዕቃ በራሱ ወጪ በሌላ ተክቶ ከሆነ ወይም በራሱ ወጪ አስጠግኖ (አሳድሶ) ከሆነ ለጉዳቱ ሐላፊ የሆነው ወገን ወጭውን ለተጐጂው እንዲተካለት ይወስናል፡፡

ሆኖም ግን ለተባለው ዕቃ መበላሸት ወይም መጐዳት ሐላፊ የሆነው ወገን መንግስት በሆነ ጊዜ የተበላሸውን ንብረት እንዲተካ ሊወሰንበት እንደማይቻል በሕጉ ላይ የተመለከተ ሲሆን በመንግስት ላይ የሚወሰነው የዕቃውን ግምት እንዲከፍል ብቻ ነው፡፡

## III. **ስለክብርና ስለመልካም ዝና (Remedial publication) ቁ.2120**

የሌላውን ሰው ክብር ወይም መልካም ዝና የሚጐዳ ተግባር ሲፈፀም ለድርጊቱ ሐላፊ የሆነው ወገን የተጐጂው መልካም ዝና ወይም ክብር ለመመለስ በራሱ ወጪ የስም ማዳሻ ማስታወቂያ እንዲገልፅና እንዲፃፍ እንዲያደርግ ዳኞች ሊያዙት እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ ለሥም ማጥፋቱ ሐላፊ የሆነው ወገን የተጐጂው መልካም ዝና ወይም ክብር እንዲመለስ በማስታወቂያ እንዲገልፅ የማዘዙ ነገር በተጐጂው ላይ ለደረሰው ጉዳት የገንዘብ ካሳ እንዲከፈለው ከሚወሰነው በተጨማሪነት ሊሆን ይችላል፡፡

ስለ መልካም ዝና ወይም ክብር በተመለከተ **በፍ/ብ/ሕግ ቁ.2120 እና 2049** መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት በሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## IV. **ማስጠንቀቂያዎች (የማገድ ትዕዛዝ) (Injunction) ቁ.2121**

አንዳንድ ድርጊቶች በባሕሪያቸ እንዲቆሙ ካልተደረገ በቀር የሚደርሰውን ጉዳት መከላከል ወይም ማስቆም አይቻልም፡፡ ለምሳሌ፡- የሌላውን ሰው ድንበር መጣስ፣ አዋኪ ነገሮችን ማድረግ ፣የሌላ ሰው መብት በሆነ የንግድ ምልክት መጠቀም እና የመሳሰሉት ድርጊቶች እንዲቆሙ ካልተደረገ በቀር ለተጐጂው መፍትሔ ላይሆን ይችላል፡፡

ስለሆነም ጉዳት የሚያመጣ ነገር እንዳይሰራ በመሰራት ላይ ካለም ድርጊቱ እንዲቆም ወደፊትም ድርጊቱን እንዳይጀምር ዳኞች የማገጃ ትዕዛዝ ሊሰጡ እንደሚችል **በፍ/ብ/ቁ.2121** ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም ዳኞች የማገጃ ትዕዛዝ የሚሰጡት ድርጊቱ ጉዳት የሚያመጣ

www.abyssinialaw.com

መሆኑን በሚገባ ሲረዱና ይህ ይደርሳል ተብሎ የሚታሰበው ጉዳት በባሕሪው በገንዘብ የማይካስ ዓይነት መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

## 4.4 በውል ሕግና ከውል ውጭ የካሳ አሰላል

ከውል ውጭ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2090 /1/ እና 2091 መሰረት ካሳው ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ መጠን ነው፡፡ የተጐጂው የጉዳት መጠን ተሰልቶ ከታወቀ በኋላ በሕጉ መርህ መሠረት ተጐጂው ጉዳቱን በሚመጥን ወይም ተመዛዛኝ በሆነ ካሳ ይካሳል ማለት ነው፡፡

ይህ የጉዳትና ካሳ ተመዛዛኝነት ከውል ውጭ ሕግ ውስጥ መሰረታዊ የካሳ ስሌት ዘዴ ሲሆን ልዩ በሆነ ሁኔታ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2098 /1/ መሰረት የደረሰው ጉዳት በተበዳዩ ክፍል ጥፋት ከሆነ ካሳው የጉዳቱ ተመዛዛኝ ሳይሆን በከፊል ብቻ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም በፍትሐብሄር ሕግ ከቁጥር 2099 እስከ 2103 የተቀመጡ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ፍ/ቤት የጉዳትና ካሣ ተመዛዛኝነት መርህን በመልቀቅ ሁኔታዎቹ የሚያመለክቱትን አነስተኛ ካሳ በርትዕ መወሰን ይችላል፡፡

በውል ሕግ ውስጥ ውል ባለመፈፀም ለሚደርስ ጉዳት የካሳው ስሌት ከውል ውጭ ሕግ ውስጥ ባሉ ድንጋጌዎች መሠረት መሆኑን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1790 /2/ ስር ተመልክቷል፡፡ ይህ የሚያሳየው የጉዳት ካሣ ተመዛዛኝነት መርህ በውል ሕግ ውስጥም ተፈፃሚነት እንደሚኖረው ነው፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1779 /1/ ስር ደግሞ ውል ባለመፈፀም የሚደርስ ኪሳራ የሚታሰበው አስተዋይ አእምሮ ያለው ሰው ውሉ ባለመፈፀሙ ይደርሳል ብሎ በሚገምተው አስተያየት ልክ መሆኑን ተደንግጓል፡፡ ይህ አስተዋይ አእምሮ ያለው ሰው አስተያየት የውል ካሳ ስሌት እላይ ለተጠቀሰው የጉዳትና ካሳ ተመዛዛኝነት መርህ ልዩ ሁኔታ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ነገር ግን በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1800 ስር ባለዕዳው በባለገንዘቡ ላይ የደረሰው ጉዳት ዝቅተኛ መሆኑን ካስረዳ እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1801 /1/ መሠረት በባለገንዘቡ ውል ሲያደርግ ጉዳቱን ይበልጥ የሚያከብዱትን ልዩ ልዩ ምክንያቶች ለባለዕዳው አስቀድሞ ያስታወቀ እንደሆነ ወይም በንዑስ ቁጥር 2 ስር ባለዕዳው ለመጉዳት ሲል ባደረገው ነገር ወይም ጉልህ በሆነ ቸልተኝነት ወይም ከባድ በሆነ ጥፋት ምክንያቶች ከሆነ የሚከፈለው ኪሣራ የሚታሰበው አስተዋይ አእምሮ ያለው

ሰው በሚገምተው አስተያየት ሳይሆን በደረሰው እርግጠኛ ጉዳት ልክ ነው፡፡ ይህ የውል አለመፈፀም ኪሳራ ስሌት ደግሞ ወደ መጀመሪያው የጉዳትና ካሳ ተመዛዛኝነት መርህ ይመልሰናል፡፡ ስለዚህ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1800 እና 1801 አነጋገር ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ጉዳት ከተረጋገጠ ካሣው በዚሁ በተረጋገጠው ጉዳት ልክ ወይም ተመዛዛኝ ተደርጐ ይሰላል፡፡ ከዚህ ውጭ በሆነ ሁኔታ ውል ባለመፈፀም የሚከፈለው ኪሳራ የሚታሰበው አስተዋይ አእምሮ ያለው ሰው ውል ባለመፈፀሙ ይደርሳል ብሎ በሚገመተው አስተያየት ልክ ይሆናል ማለት ነው፡፡

## የወንጀል ተጠቂዎችና የካሳ ጥያቄ

በወንጀልም ሆነ ወንጀል ባልሆነ ድርጊት ከውል ውጭ የሆነ ጉዳት የደረሰበት ሰው ለደረሰበት ጉዳት የካሳ ጥያቄውን ከውል ውጭ ሕግ ድንጋጌዎች ላይ በመመስረት ማቅረብ ይችላል፡፡ የካሳ ጥያቄውም የፍትሐብሔር ጥያቄ ከመሆኑ የተነሳ የሚቀርበው የፍትሐብሔርን ጉዳይን ለማየት ስልጣን ለተሰጠው ፍርድቤት ነው፡፡

ነገር ግን ከዚህ በተለየ ሁኔታ በወንጀል ጥቃት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ ከቁጥር 154 እስከ 159 ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት የካሳ ጥያቄውን ከወንጀሉ ክስ ጋር የወንጀል ክሱን እያየ ላለው ፍ/ቤት አቅርቦ እንዲታይለት ማድረግ ይችላል፡፡

ከወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች ለመረዳት እንደሚቻለው የካሳ ጥያቄው ከወንጀል ክስ ጋር እንዲቀርብ የተፈቀደበት ምክንያት በወንጀል ጥቃት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው ለተጨማሪ ወጪ ሳይደረግ ለምሳሌ የዳኝነት ክፍያ፣ ከወንጀሉ ምስክሮች ተጨማሪ ካልሆነ በስተቀር የመጥሪያ ክፍያ ሳይከፍል የካሳ ጥያቄው በፍጥነት ታይቶ ውሣኔ እንዲያገኝ ነው፡፡ /የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154እና 159 /.

ይህ የካሳ ጥያቄ ስነስርዓት በወንጀል ተጠቂዎች ጥቅም የተቀመጠ ከሆነም በወንጀል ጥቃት ምክንያት ጉዳት የሚደርስባቸው ሰዎች የካሳ ጥያቄአቸውን ለየብቻ ለፍትሐብሔር ችሎት ማቅረብ እንጂ ከወንጀል ክስ ጋር አያይዘው

www.abyssinialaw.com

የወንጀሉን ክስ ለሚያየው ችሎት ማቅረብ በስራ ላይ እምብዛም አልተለመደም፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 12667 ላይ በመኪና ግጭት የ13 ዓመት ልጅ የሞተባት እናት ልጄ በሕይወት እያለ እየተላላከልኝ ድንችና ቃሪያ እየሸጠ ገቢ ያስገኝልኝ ነበር፡፡ አሁን ይህ የልጄ እርዳታና ገቢ ስለቀረብኝ ካሣ ይከፈለኝ ብላ ያቀረበችውን ጥያቄ ሟቹ ልጅ ከወላጅ እናቱ እርዳታ የሚፈልግ ታዳጊ ሕፃን ነው እንጂ እናቱን ሊያስተዳድር የሚችል አይደለም በማለት ጥያቄዋን ውድቅ አድርጓል፡፡

   ሠልጣኞች የፍ/ቤቱን ውሳኔ ከሕጉና በተለምዶ በሀገራችን ልጆች በቤተሰብ ውስጥ ካላቸው የሥራ ድርሻ አንጻር እንዴት ትገመግማላችሁ?

2 የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 1128 የ9 ዓመት ሕፃን በመኪና ተገጭታ በእግሯና በእጇ ላይ ቋሚ የአካል ጉዳት ስለደረሰ በሕፃኗ ሞግዚት በቀረበ የካሣ ክስ ላይ በሰጠው ውሳኔ በሕፃኗ መጎዳት አሁን የቀረ ገቢ ባይኖርም ሕፃኗ ወደፊት ሙሉ አካል እንዳለው ሰው ሰርታም ሆነ ተሯሩጣ ኑሮዋን ለማሸነፍ የነበራት አቅም በእጅጉ የሚቀንስ ስለሆነ ይህ ጉዳት ደግሞ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ማወቅ አስቸጋሪ ስለሆነ በማለት የወደፊት ጉዳት ካሣን በርትዕ ለሕፃኗ ወስኗል፡፡በውሳኔው አግባብነት ላይ ተወያዩበት

3 በሌላ ፍ/ቤት በቀረበ የወደፊት ጉዳት ካሣ ጥያቄ የኮሌጅ ተማሪ የሆነ ልጅ በመኪና ግጭት የሞተችባቸው ቤተሰብ ይህ ልጃቸው ትምህርቱን ጨርሶ ጥሩ ሥራ ላይ በመሰማራት ሊጦራቸው የሚችል ስለሆነ አሁን ግን ይህ ስለቀረባቸው ካሣ ታስቦ እንዲከፈላቸው ጠይቋል፡፡

   ሠልጣኞች ለዚህ ጥያቄ አግባብነት ያለውን ምክንያት በመሰንዘር የውሳኔ አስተያየት ስጡበት፡፡

4. ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.19338 ላይ በቀረበ ጉዳይ አመልካች በመጀመሪያ በምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተካሳሽ(ተጠሪ) ላይ ባቀረበችው ክስ ተካሳሽ ባደረሰብኝ ድብደባ ቀኝ አይኔ የጠፋ ሲሆን በአይኔ ላይ የደረሰውን ጉዳት በህክምና ለመከታተል ከሚረደኝ አንድ ሰው ጋር በመሆን ወደ አዲስ አበባ ስንመላለስ ለትራንስፖርት ብር 2950.90 ለሆስፒታልና ለመድኃኒት ብር 363.16 ለሰው ሰራሽ አይን ማስተከያና ለመነጽር ብር 415.00 ለምግብ ለአልጋና ለታክሲ ብር 8100.00 ወጪ የሞራል ካሳ ብር 1000.00 ይከፈለኝ በተጨማሪም ዓይኔ ሲጠፋ 10ኛ ክፍል የደረስኩና ዕድሜዬ 20 ዓመት የነበረ ሲሆን በጉዳቱ ምክንያት ትምህርቴን በማቋረጤ የመንግስት ሰራተኛ የመሆን ፍላጎቴ እውን ሊሆን ባለመቻሉ ዓይኔ ባይታወር ኖሮ በትንሹ በወር ብር 120 በማግኛት የመንግስት ስራን እስከ 55 ዓመት ብሰራ 35 ዓመት በስራ ላይ እቆይ የነበረ በመሆኑ ይህም ሲሰላ 120x12x35= ብር 40,000.00 ስለሚሆን በአጠቃላይ ብር 50,830.56 ከወጪና ኪሳራ ጋር ይከፈለኝ ብላ ከሳለች፡፡

የዞኑ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመልከት ከሳሽ በደረሰባት ድብደባ አንድ አይኗን ያጣች ስለሆነና አንድ ዓይን ያለው ሰው ሁለት ዓይን ካለው ሰው ጋር እኩል የመስራት ችሎታ እንደማይኖረው ይታመናል በማለት ከሳሽ ጉዳቱ ሲደርስ ዕድሜዋ 27 ዓመት የነበረ ሲሆን ጉዳቱ ባይደርስባት ኖሮ በቀን ብር 4 በወር ብር 120 በዓመት ብር 1440.00 ማግኘት ትችላለች ከሳሽ እስከ 50 ዓመት ድረስ ትኖራለች ተብሎ ስለሚገመት በአጠቃላይ ብር 41,760.00 ገቢ ተገኝ ነበር፡፡

ይሁንና በደረሰባት ጉዳት ምክንያት 40% የመስራት አቅሟ የቀነሰ ስለሆነ ይህም ሲሰላ ብር 16,800.57 ስለሚሆን የሞራል ካሳ ብር 1000.00 ጨምሮ ብር 17,800.00፣ ለመድኃኒት መግዣ ብር 363.05 ለመነጽር ብር 415.40 ለትራንስፖርት ብር 1060.30 በአዲስ አበባ ቆይታ የአልጋ የምግብና የታክሲ ከሳሽንና ረደቷን ጨምሮ ብር 1740.00 በአጠቃላይ ብር 21,378.92 ተከሳሽ ለከሳሽ ይክፈል ብሎ ወስኗል፡፡

ተከሳሽ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ተከሳሽ ይህንን ጉዳይ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሲያቀርብ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ከሳሽ በአንድ አይኗ መጥፋት ምክንያት ሰረታ ገቢ ለማግኛት የሚከለክላት ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የወደፊት ጉዳት ካሳ ሊከፈላት ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/2090(1) አኳያ ተገቢ አይደለም በማለት በዚህ ረገድ የተወሰነውን የካሳ ክፍያ በመሻር ህክምናውን

ለመከታተል ከሳሽ ያወጣችውን ወጪና የሞራል ካሳን በተመለከተ እንዲከፈላት የተወሰነውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ውሳኔውን በመቃወም የስር ካሳሽ(አመልካች) ጉዳዩን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሲታቀርብ ችሎቱም አመልካች በደረሰባት የአንድ አይን መጥፋት ምክንያት ሙሉ ለሙሉ የመስራት ችሎታዋን አጥታለት ባይባልም ካሳ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን አለበት ሲባል በአጠቃላይ የመስራት ኃይል ቅነሳ (General utility) ጋር ተገናዝቦ እንጂ ከልዩ የመስራት ኃይል ቅነሳ (special utility) ጋር ተገናዝቦ ባለመሆኑ አመልካች አንድ አይኗን ማጣቷ በወደፊት ሕይወት የገቢ መጠን መቀነስ ባያስከትልም እንኳን በአጠቃላይ እንደ ሰው ለመኖር በእያንዳንዱ የእለት ሕይወቷና እንቅስቀሴ ላይ ጉዳት መድረሱ ምክንያታዊ እርግጠኛነት (Reasonable certainty) ያለው በመሆኑ ካሳን መወሰኑ ከቁጥር 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች አንፃር ካሳን መወሳን አግባብነት ይኖራዋል፡፡ ጉዳት የደረሰባት ወገን የደረሰበትን ጉዳት ልክና ጉዳት አድራሹ ካሳ በመክፈል ረገድ ያለበትን ግዴታ ማስረዳት እንደለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2141 ላይ የተመለከተ ቢሆንም ተጎጂው ጉዳት የደረሰበት መሆኑን አረጋግጦ ነገር ግን የካሳውን መጠን ለመገመት አስቸጋር ሁኔታ በሚያገጥም ጊዜ በቁጥር 2102 መሰረት ዳኞች የካሳውን መጠን በርትዕ ለመወሳን ስልጣን የተሰጣቸው ስለሆነ የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የካሳውን መጠን በርትዕ መወሳኑ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ማጽናቱ አግባብነት ያለው ነው በማለት ለአመልካች የወደፊት ካሳ ሊከፈል አይጋባም ተብሎ የተወሰነውን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሽሮአል፡፡

- በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሳኔዎች በመመልከት የትኛው ውሳኔ ህጉን በአግባቡ የተከተለ ይመስላችኃል? በምክንያት በማስደጋፍ አብራሩ
- የምዕራብ ወላጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ካሳሽ(አመልካች) 50 ዓመት ሊትኖር ትችላለች ብሎ ያስቀመጠው ምንን ምክንያት በማድረግ ነው?
- የምዕራብ ወላጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ 40% የአካል ጉዳት ደርሶባታል የሚለውን ማስረጃ በቀጥታ ከገቢ ጋር በማገናኘት የወደፊት የአመልካች ገቢ በዚሁ መጠን ይቀንሳል ብሎ ያስቀመጠው ስሌት ትክክል ነው ብላችሁ ታምነላችሁ? የህክምና ቦርድ የሚወስነው የአከል ጉድለት መጠንና የተጎጂው የመስራት አቅም እንዴት ይዛመደል?

5. በአንድ ፍ/ቤት በቀረበ ሌላ ጉዳይ ደግሞ ባለቤቱ በመኪና አደጋ የአካል ጉዳት ስለደረሰባት ባል እሷን ለማስታመም ሐኪም ቤት በተመላለስኩበት ወቅት በንግድ ስራዬ ላይ በመሰማራት በየቀኑ አገኝ የነበረው ገቢ ስለቀረብኝ ይኸው ይከፈለኝ ብሎ ለባለቤቱ ጉዳት ኃላፊ በሆነው ሰው ላይ ክስ አቅርቧል፡፡

የደረሰው አደጋና የተጠየቀው ካሳ ግንኙነት አለው? ይብራራ::

6. ወ/ሮ አለሚቱ የ40 ዓመት ሴት በግል የፅሕፈት ሥራ ድርጅት በታይፒስትነት ተቀጥራ በመስራት በወር 500 (አምስት መቶ ብር) ደሞዝ ይከፈላታል:: ወ/ሮ አለሚቱ ከሥራ ወደ ቤት በእግር በመጓዝ ላይ እያለች የአቶ እንግዳ ንብረት የሆነ መኪና ወ/ሮ አለሚቱን ገጭቶ የወ/ሮ አለሚቱ የቀኝ እጅ መሐል ጣት ክፋኛ ተጐድቶ እንዲቆረጥ ተደረጓል:: በዚህም ሳቢያ ወ/ሮ አለሚቱ በታይፒሲትነት ሥራ (ሞያ) መቀጠል አልቻለችም::

ሀ. ለወ/ሮ አለሚቱ የሚከፈላት የጉዳት ካሳ እንዴት ይሰላል?

ለ. ለወ/ሮ አለሚቱ የሚከፈላት የጉዳት ካሳ 100% ጉዳት እንደደረሰበት ሰው ተቀጥሮ ይከፈላት የነበረው ደሞዝ እና እድሜዋ ተዝናዝቦ በ100% ጉዳት ነው? ወይንስ ምንም እንኳ ጣቷ በመቆረጡ በታይፒስትነት ሞያ መቀጠል ባትችልም በሌላ ሥራ የመሰማራት እድሉ ያላት መሆኑ መገናዘብ ይኖርበታል? ይብራራ!

7. አንድ የ 8 ዓመት ታዳጊ ልጅ የመኪና አደጋ ደርሶበት አንድ አይኑ ላይ ጉዳት ደርሶበት ቢጠፋ በፍ/ብሔር ሕግ ቁ.2092 መሠረት የወደፊት ጉዳት ካሳ መጠየቅ ይችላል:: ወይ?

- በፍ/ብሔር ሕግ ቁ.2092 ......ጉዳቱ የተረጋገጠ ሲሆን ... የሚለው ሐረግ ከፍ/ብሔር ቁ.2102 ድንጋጌ ጋር እንዴት ይዛመዳል?

8. በፍ/ብሔር ሕግ ቁ.2095 መሠረት ለሞት አደጋ ካሳ የሚከፈለው ምግብን ወይም መተዳደሪያን በመስጠት እንደሚደረገው ጡረታ መልክና ዓይነት መሆኑ ተደንግጓል:: ሆኖም ግን በኢትዩጵያ ፍ/ቤቶች ለሞት አደጋ የሚከፈለው ካሳ በጡረታ መልክና ዓይነት ሳይሆን በአንድ ጊዜ የተወሰነ ገንዘብ (Lump sum) ለተጐጂዎቹ እንዲከፈል በማዘዝ (በመወሰን) ነው::

ሀ. በጡረታ መልክ እና ዓይነት የጉዳት ካሳው እንዲከፈል ማድረግ ከተጐጂዎቹ እና ከካሳ ከፋዩ አንፃር ያለው ጠቀሜታና ጉዳት አብራራ?

ለ. የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ለሞት አደጋ የጉዳት ካሳ አከፋፈል ላይ በሕጉ ከተመለከተው ሥርዓት ውጪ በአንድ ጊዜ የተወሰነ ገንዘብ (Lump sum) እንዲከፈል የሚወስኑት ለምን ይመስለሃል?

9. **በፍ/ብሔር ሕግ ቁ.2116 (3)** መሠረት የሕሊና ጉዳት ካሳ በማናቸውም ምክንያት ከ1000 (አንድ ሺህ ብር) የበለጠ ሊሆን እንደማይችል ተደንግጓል። የሕሊና ጉዳት ካሳ ጠያቂወች ከአንድ ሰው በላይ በሆኑ ጊዜ ለእያንዳንዳቸው እስከ 1000 (አንድ ሺህ ብር) እንዲከፈላቸው መወሰን ይቻላል? ለምን?

# ማጠቃለያ

ይህ ጽሑፍ ከውል ውጪ ለሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ሕግ ዋና ዋና ነጥቦችን በማንሳት በአሠራር ላይ ተደጋግሞ በሚያጋጥሙ ጉዳቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን በየክፍሉ የተነሱ የፍርድ ቤት ጉዳዮችና ጥያቄዎች ሕጉን በስፋት የዳሰሱ ናቸው፡፡

ለሠልጣኞች ሥልጠና የተዘጋጀ ሥራ ስለሆነ ሃሳቦችን በመተንተን በማብራራት ከመጨረስ ይልቅ ለውይይት በሚጋብዝ መልኩ ማቅረብ ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ ሠልጣኞች በየክፍሉ በተነሱ ጉዳዮች ላይ በትኩረት መወያየትና ጥያቄዎቹን መሥራት አለባቸው፡፡

አሠልጣኙም በየክፍሉ በተነሱ የውይይት ነጥቦች ላይ ሠልጣኞች በትኩረት እንዲሳተፉ በማነሳሳት የክንውን ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በማድረግ እንዲሁም በመፍትሔ ሃሳቦች ላይ ሠልጣኞችን በመምራት ሥልጠናው ግቡን እንዲመታ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

# ዋቢ መጽሐፍቶች


1. የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ
2. የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ
3. የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ
4. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔዎች ቮልዩም 1 ቁጥር 1
5. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ውሳኔዎች ቮልዩም 1 ቁጥር 1
6. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔዎች ቮልዩም 3 ቁጥር 3
7. JERZ (GEORGE) KRZECZUNOWICZ, (1977)

   The Ethiopian Law of Compensation for damage

   Addis Ababa University Faculty of Law: